Ee-JRIF
Ethiopian e-Journal for Research and Innovation Foresight

Vol. 9. no. 1, (2017) : pp (134 – 152)

# አድዋ፥ ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች[1] የመቶ ሃያ አንደኛው የ (፻፳፩) ኛው ዓመት የድል በሃል፥ ኢትዮጵያን ለድል ያበቃው አንድነትና አመራር

ለምለም ተሊላ
Managing Editor of Ee-JRIF and NES-GLOBAL

"*... እኛ ግን እንኳን ልእልፍና ለሁለት እልፍ ሰው የኢጣሊያ ሀገር ሰው ሁሉ ቢመጣ የኢጣሊያን ጥገኝነት ይቀበላሉ ብለህ አትጠርጥር.*" አጤ ምኒልክ ነሐሴ 23 ቀን 1887 ዓ.ም. አውሮጳ ለነበረው ለሙሴ እልግ ከጻፉት የግል ደብዳቤ ላይ።[2]

"*...እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ. . .*" እቴጌ ጣይቱን ጠቅሶ ሳሊምቢኒ በ1890 ዓ.ም. እንደጻፈው።[3]

## መግቢያ

በአስራ ስምንተኛው ምህተ ዓመት በዘመናዊ የጦር ሃይል የታጠቀና በሰለጠነ የጦር ሰራዊት የተደራጀ፥ የቅኝ ግዛትና የመስፋፋት ህልም ያለውን፥ የወራሪው ጣሊያንን ኃይል አንዲት አፍሪካዊት ሀገር አድዋ ላይ አሸንፋ ድል ለመቀዳጀት ያስቻላት የንጉሰ ነገስቱና የሕዝቡ በአንድነት መቆም ትልቅ ድርሻ ነበረው። በተለይም ሕዝቡ ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ ከምህራብ እስከ ምስራቅ፥ ከጫፍ እስከጫፍ በጋራ ጠላትን ለመመከት በአንድነት መነሳት በመቻሉ ነው። ይህ ጽሑፍም የአድዋው ጦርነት መንስሔውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ወራሪው ጣሊያንን ለመመከት በጋራ በአንድነት የተሰባሰበበትንና የዘመተበትን መንገድ በማጤን፥ የአድዋው ጦርነትና ታላቁን ድል በመቃኘት አድዋ ላይ ዋናው የጦሩ መሪ የነበሩት ንጉሰ ነገስቱና አማካሪዎቻቸው በጦርነቱ ወቅትም ሆነ ከዚያ በፊት በሀገር ጉዳይ ላይ ያሳለፏቸውን ውሳኔዎችና የወሰዱዋቸውን እርምጃዎች ከንጉሰ ነገስቱ የግል ስብዕናቸው ጋር በማነጻጸር፥ ከድሉ በኋላ ኃያላኑ የአውሮጳ ሀገራትን ጨምሮ የኢትዮጵያ ወዳጆችም ሆኑ ጠላቶች ድሉን አስመልክቶ በኢትዮጵያና በንጉሰ ነገስቱ አጤ ምኒልክ ላይ በወቅቱ የወሰዱዋቸውን ውሳኔዎች ይዳስሳል።

ለአድዋው ጦርነት ዋናው የጦርነቱ ሰበብ የነበረው የውጫሌ ውል ተብሎ የሚጠራው ውል ነው[4]። ይህም በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ (፲፰፻፹፩) ዓ.ም. ከንጉሰ ነገስቱ አጤ ዮሐንስ ሞት በኋላ አጤ ምኒልክ ሀገራቸውን ለማረጋጋት እየተዘዋወሩ በነበሩት ሰዓት ወሎ ድረስ በመሄድ፥ ውጫሌ ላይ በጉዞዋቸው ላይ እንዳሉ፥ ኮንቲ አንቶኔሊ የተባለው

የጣሊያን መልህክተኛ ተሯሩጦ ያስፈረማቸው ውል ሲሆን፥ የዉሉም አስራ ሰባተኛው (፲፯ኛው) አንቀጽ በአማርኛና በጣሊያንኛው ትርጉም መፋለስ ምክንያት ነው። አስራ ሰባተኛው አንቀጽ በአማርኛው የሚለው "*የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከአውሮጳውያን ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በጣሊያን መንግስት ኢጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል*" ሲል፥ በጣሊያንኛው ግን "*የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ ሀገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በጣሊያን መንግስት አማካይነት ማድረግ ይገባዋል*"[5] የሚል በመሆኑ የጣሊያንኛው ትርጉም የኢትዮጵያን በጣሊያን ስር ጥገኛ መሆን የሚያመለክት ሲሆን የአማርኛው ግን ኢትዮጵያ የጣሊያን እገዛ ሲያስፈልጋት ብቻ እንድምታገኝ የሚያረጋግጥ፣ የመረዳዳትና የመልካም ግኑኝነት ብቻ ነው። በእርግጥም በወቅቱ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስትና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ብጡል ውሉን ሲፈራረሙ የጣሊያንን ድብቅ

---

[1] https://www.youtube.com/watch?v=3fgZDgOOipk https://www.youtube.com/watch?v=-FjPmCVYRvU

[2] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 139)

[3] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ (ገጽ 148)

[4] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት (ገጽ 196)

[5] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ (ገጽ 211) ፥ ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 140)

ሴራ አልተረዱትም ነበር። በጣሊያን በኩል ግን ውሉን ከተፈራረሙበት ዕለት እ.ኤ.አ. ከአክቶበር አስራ አንድ (፲፩) ቀን ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ (፲፰፻፹፱) ዓ.ም. ጀምሮ "***ኢትዮጵያ በጣሊያን ስር ነች***"[6] በማለት ለአስራ ሁለት የአውሮጳ ሀገራትና ለአሜሪካም ጭምር የእወቁልኝ ዓይነት ደብዳቤ ጽፎ ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት ግን የጣሊያንን ድብቅ የመስፋፋትና የቅኝ ግዛት ህልም ማወቅ የቻለው ኢትዮጵያ የአጤ ምኒልክን የንግስናቸውን ዜና ለማሳወቅ ለአውሮጳ ሀገራት ደብዳቤ በምትላላክበት ጊዜ የጣሊያን መሪ ንጉስ ኡምቤርቶ '***ኢትዮጵያ ከሌሎች አውሮጳውያን ሀገራት ጋር በቀጥታ መላላክ የለባትም ደብዳቤው በጣሊያን በኩል ማለፍ ነበረበት***' በሚል አምባጓሮ ሲያስነሳ ነው። በተለይም በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ሁለት (፲፰፻፹፪)[7] ዓ.ም ኃያላን የአውሮጳ ሃገራት "*የባርያ ንግድን ለማስቀረት*" በነበራቸው ጉባኤ ላይ ጣሊያን "***ኢትዮጵያን ወክዬ የምቀርበው እኔ ነኝ***" ማለቷ ሳያንስ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ቤልጅየም፣ ኦስትሪያና ሌሎቹም የአውሮጳ ሃገራት *የጣሊያን መንግስት "ለኢትዮጵያ ተወካይ ቢሆን አንቃወምም"* በሚል የጣሊያንን ፍላጎት በድምጽ ብልጫ ማጽደቃቸው ኢትዮጵያ እራስዋን የቻለች፥ የማንንም ፈቃድ የማትጠብቅ፥ ሉዓላዊት ሀገር መሆንዋን መናቅ ለአጤ ምኒልክ እጅግ አስደንጋጭ ነበር።

በመሆኑም ንጉሱና ንግስቲቱ ይህንን የጣሊያንን ድብቅ ፍላጎት ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ የውሉ አስራ ሰባተኛው አንቀጽ እንዲስተካከል በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ጣሊያን ግን በሰው፣ በገንዘብ፣ በአውሮጳውያንና በመልህክተኞችም በማታለልና በንቀት አንቀጹን ላለማስተካከል ያላደረገው ሙከራ የለም። አጤ ምኒልክና ባለቤታቸው ግን የሀገራቸውን ሉዓላዊነት ላለማስደፈር የነበራቸውን ጠንካራ አቋም በተግባርም በክርክርም ለማስረዳት የሄዱባቸው መንገዶች፥ ፍጹም ቆራጥነት የተሞላበትና የወራሪውን ህብሪት ፊት ለፊት ተጋፍጠው በድፍረት በመንገር የገለጹባቸው ታሪካዊ እውነቶች፥ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው የጥቁር ሕዝብ ለዘላለም አኩሪ ሆነው፥ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ ታላቅ እሴቶች በመሆናቸው ኢትዮጵያን ለድል ያበቃው የንጉስ ነገስቱና የንግስቲቱ ጽኑህ፥ ታላቅ አመራር ሕዝባቸውን ከዳር እስከዳር ማንቀሳቀስ የቻለ ነበር። አጤ ምኒልክ ይህ የውል ሰነድ እንዲስተካከል በደብዳቤም በሰውም በተደጋጋሚ ቢጠይቁም በተቃራኒው ጣሊያን ግን የኢትዮጵያን መንግስት የመደለል ሙከራው ስላልተሳካላት በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ (፲፰፻፹፩) ዓ.ም. ውጫሌ ላይ ዉሉን ያስፈረመውን የጣሊያን መንግስት መልህክተኛ የሆነው ተልኮ ለመጨረሻ ጊዜ ለመደራደር በሚዘጋጁበት ሰዓት እቴጌ ጣይቱም ከመልህክተኛው ጋር የሚደረገው ውይይት ላይ ገብተው ሲከራከሩ ለአንቶኔሊ የቅኝ ግዛት ሙከራ አልበገር በማለት የአስራ ሰባተኛው እንቀጽ ጨርሶ ተሰርዟል በማለታቸው መልህክተኛው ከመናደዱ የተነሳ ምኒልክን "***ስልጣናቸውን ሁሉ ለሴት ለቀው ያላግጡብናል***"[8] ብሎ መናገሩ ተዘግቧል። ምክንያቱም አጤ ምኒልክ ደም እንዳይፈስ ብዙ ሙከራ እያደረጉ ሳለ አንቶኔሊ የሚፈልገው የኢትዮጵያን በጣሊያን ጥገኝነት ስር መውደቅ በመሆኑ፥ እቴጌይቱ ነጻነትን አሳልፎ ላለመስጠት ምንም ዓይነት የጣሊያን ሙከራ እንዳይሰካ ያደረጉ ሴት በመሆናቸው፥ በምኒልክ ስርወ መንግስት የነበራቸው ድርሻ ትልቅ አስተዋጾ እንደነበረው ነው መልእክተኛው የመሰከረው። በተጨማሪም በክርክሩ ወቅት ኮንት አንቶኔሊ የቅኝ ግዛትና የመስፋፋት ስሜቱን መደበቅ ስላልቻለ በአጻፋው ንጉሱና ንግስትቲቱም አፍሪካዊ ጽናታቸውን በድፍረት በመግለጽ፥ ለወራሪው እንደማይበገሩለት በማረጋገጣቸው፥ በተለይም እቴጌይቱ መልህክተኛው የውሉን ወረቀት መቅደዱና የጦርነት ዛቻውን በሰሙ ጊዜ "***የዛሬ ሳምንት ኢድርገው የሚደነግጥልህ የለም***" በሚል ምላሻቸውን ከመስጠት አልፈው "***እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነት እመርጣለሁ***" ማለታቸውን ሳሊምቢኒ የተባለው ሌላው የጣሊያን መልህክተኛ እ.ኤ.አ. በአስራ ስምንት መቶ ዘጠና (፲፰፻፺ ዓ.ም. የጻፈውን በመጥቀስ ጳዉሎስ ኞኞ ዘግቦታል። እንኳን ድሮ (ጥንት) በአስራ ስምንተኛው ምህተ ዓመት፥ ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በዓለም ላይ በሀገር ጉዳይ የመሪነት ቦታው ላይ የሴቶች ድርሻ ከወንድ እኩል ባልሆነበት ዘመን፥ የጥንቷ ኢትዮጵያ ግን በአስራ ስምንተኛው ምህተ ዓመት ሴቶችን በአመራር ላይ ያስቀመጠች ብቻ ሳትሆን በውሳኔ ላይም ሴቶች ድምጽ እንደነበራቸው አድዋ ላይ ያስመሰከረች ኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ አፍሪካዊት ሀገር ነች። ጣሊያን ኮንት አንቶኔሊን በዋና መልእክተኛነት የውጫሌ ውልን ለይምሰል እንዲደራደር ቢልክም፥ እራሱ ሳሊምቢኒን ግን ውሉ ባለበት እንዲጸና እንዲያደርግ መታዘዙን ጠቅሷል። በተለይም በስተመጨረሻ ላይ ከመልህክተኛው ጋር ሲደራደሩ ሙከራው በሙሉ በዕለቱ እንዳልተሳካለት ሲያውቅ በንቀት ያደረገው ሙከራ "***ውሉ ለአምስት ዓመት ብቻ ስለሆነ ሶስት ብቻ ነው የቀረንና እንጠብቅ***" የሚሉ የማታለያ ቃላቶች ሲወረውር ምኒልክ ትዕግስታቸው በማለቁ የሰጡት ምላሽ:

> "***እንዲህ ነገሩ ሳይጎላ እንዲህ ባጓጉል እንኳን ሶስት ዓመት ሶስት ቀንም ቢሆን አያድርምና ይልቁንስ አሁን ቶሎ ይለቅ***"[9] በማለት ነው ቁርጡን የነገሩት።

በመሆኑም ምኒልክ በቆራጥነት በዘመናዊ የጦር መሳሪያና በሰለጠነ ወታደር የተደራጀውን የወራሪውን የነጭ ጦር በዚያ ዘመን እንኳን ሶስት ዓመት የሶስት ቀናትም ጊዜ እንደማይሰጡት አስረግጠው በመንገር ያላቸውን ጠንካራ አቋምና

---

[6] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 143)

[7] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ (ገጽ 144-148)

[8] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት (ገጽ 213-215)

[9] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 146-150)

የሀገራቸውን ሉዓላዊነት እንደማይደራደሩ ነው ያረጋገጡት። አንቶኔሊ የመጨረሻው ሙከራው ለማሳመንም ሆነ ለማታለል ስላልተሳካለት ተናዶ ሲወጣ የሚሄድበት በቅሎ እንዲሰጠው ያዘዙ ስልጡን መሪ ናቸው። እንደጳዉሎስ ኞኞ አገላለጽ የውጫሌ የውል ሰነድ '*የተቀደደው በመድፍ*' ነው። ከዚህ ታሪካዊ የንጉሰ ነገስቱና የእቴጌዪቱ ምላሽ የምንገነዘበው ቁም ነገር ቢኖር ልክ እንደወንዶቹ የኢትዮጵያ ሴቶች በነበራቸው አስተዋይና ብልህ አመራር በሀገር፣ በወገንና በማንነታቸው ላይ ለተነሳ ለውጪም ሆነ ለውስጥ ሃይል እንደማይበገሩ በተለያዩ መንገዶች ይገልጹ እንደነበር ያረጋግጣል።

ለአድዋው ጦርነት መነሻው የውጫሌ ውልም ሆነ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ከአጤ ምኒልክ በሳልና አስተዋይ አመራር በተጨማሪ እቴጌይቱም ያሳዩት ቆራጥነት የሚያመለክተው በጊዜው ኢትዮጵያውያን ሴቶች የነበራቸውን ቦታ በግልጽ ከማሳየቱ በተጨማሪም የጥንት ኢትዮጵያውያን ወንድ ገዢዎችም ሴቶቹን በሴትነታቸው ሳይንቁዋቸው በምክርም ሆነ ውሳኔ በመስጠት ድርሻቸው ያከብሩዋቸው እንደነበርና ባጠቃላይ የኢትዮጵያውያንን ስነ ልቦና የተለየ ከፍተኛ ግምት የሚያሰጠው ታላቅ እሴት ነው። ከእቴጌ ጣይቱ በፊትም ጥንት የነበሩትን የኢትዮጵያ ነገስታት ስንፈትሽ የጥንትዋ ኢትዮጵያ በኩሽ ነገድ ስም የኩሽ ምድር፣ በኩሽ ልጆችም (በሳባ ስም የሳባ ምድር፣ በአቢስ ስም አቢስንያ) ስትባል ቆይታ በመጨረሻ አባታቸው ኩሽ ከሞተ ከሁለት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ዓመታት በኋላ ማለትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለት መቶ ሃምሳ አራት ዓመተ ዓለም (፪፻፶፬ ዓ.ዓ) በአባታቸው በኩሽ በሁለተኛው ስሙ በ'*ኢትዮጵ*' ስም ኢትዮጵያ[10] ብለው ከመሰየማቸው በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ከነገሱት ነገስታት ውስጥ ሴቶችም ይገኙበት ነበር። ከነኚህም መሀል ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሰላሳ አራት (፴፬) ዓ.ም. የነገሰችው ሰባ ሶስተኛዋ ገዢ (፸፫ኛዋ)[11] ንግስት ገርሳሞት ህንደኬ ሰባተኛ (፯ኛ) የተባለችው ወሰንዋን ተሻግራ ባሁኑ ፓለስታይን በጋዛ የራሷ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሾማ እንደነበር በቅዱስ መጽሐፍም[12] ተጠቅሷል። ከእርሷም በኋላ የተለያዩ ሴት ነገስታት ነግሰዋል። በአጤ ቴዎድሮስ ስርወ መንግስት ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር በሺህ ስምንት መቶ አርባ ስድስት (፲፰፻፵፮) ዓ.ም. ለጦርነት ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ የሸዋው ንጉስ ኃይለ መለኮት ሞተው ስለነበር ልጃቸው ምኒልክን[13] በአስር ዓመቱ አስረው ወስደውት ነበር። ነገር ግን ህጻኑ ምኒልክ ሲያድግ ከታሰረበት አምልጦ ወደ ወረይመኑዋ ገዢ፥ ወደ ወይዘሮ ወርቂት ግዛት ስለገባ አጤ ቴዎድሮስ ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ከባድ ውጊያ አድርገዋል። ልክ እንደ ህጻን ምኒልክ የወይዘሮ ወርቂት ልጅም የአጤ ቴዎድሮስ እስረኛ ስለነበር ንጉሱ በምኒልክ ንዴት የወርቂትን ልጅ ቢገሉባቸውም ወይዘሮዋ ግን የንጉሱ ሃይለኛነት ሳይበግራቸው ምኒልክን አሳልፈው ያልሰጡ ሲሆን፥ እንዲያውም ወደ ዘመዶቹ ወደ ሸዋ የላኩ አስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ያፈራቸው የወረይመኑ ገዢ የነበሩት ወይዘሮ ወርቂት ሌላዋ ደፋር ጠንካራና ቆራጥ ሴት፥ የኢትዮጵያ ሴቶች ከአድዋው ጦርነት በፊትም ጉልህ ድርሻ እንደነበራቸው ያረጋግጣል። በአጤ ምኒልክ ስርወ መንግስትም ልክ እንደጥንቶቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች እቴጌይቱም ያሳዩት ቆራጥነት የሚያመለክተው ልክ እንደንጉሰ ነገስቱ በዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን ሴቶችም በዘመናዊ የጦር መሳሪያና በሰለጠነ ወታደር የተደራጀውን የወራሪውን የነጭ ጦር በሀገራቸው ሉዓላዊነት እንደማይደራደሩ ነው ያረጋገጡት።

አንዲት አፍሪካዊት ሀገር በዘመናዊ የጦር መሳሪያ በታጠቀና በሰለጠነ የጦር ሃይል የተደራጀን፣ ተስፋፊና ቅኝ ገዢ፣ የወራሪውን የጣሊያንን ሃይል በባህላዊ የእጅ ጥበበበኞች ስራ በምታፈራው የጦር መሳሪያ (በጦርና በጎራዴ፣ በጨቤና በአንካሴ፣ በጦርና በጋሻ) በመመከት ከመቶ ሃያ ዓመታት በፊት እንደ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (፲፰፻፹፰) ዓመት ምህረት የወራሪው፣ የቅኝ ገዢውን ዕቅድ በማክሸፍ ጣሊያንን ያስበረገገች፣ ዓለምን ያስደመመች፣ ምህራባውያንን ያስደነገጠች፣ አውሮጳውያን ጀርመን በርሊን[14] ላይ አፍሪካን ለመቀራመት ያቀዱትን ዕቅድ ደግመው እንዲያጤኑት ያደረገች[15]፣ ብቸኛዋ በዓለም ታሪክ ጸሐፊዎችና በሊቀ ሊቃውንቶች አድዋ ላይ ድል ማድረጓ የተመሰከረላት፣ ድል የተቀናጀችበትን የድል በሃሏን ከአጋሮችዋና ከነጻነት ናፋቂው የዓለም ሕዝብ ጋር በጋራ የምታከበረው የአድዋው ድል ባለቤት፣ ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካውያን የነጻነት አርማ ስትሆን፣ ኢትዮጵያዊነት ደግሞ ፕሮፌሰር ሐሰን ሁሴን ሚኒሶታ ላይ ከጠቀሱት ብንዋስ[16] "*ኢትዮጵያዊነት የዘር ሐረግ ቆጠራ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ታሪክ፣ ሕግ፣ ፍልስፍናና*

---

10 አባ ጎርጎሪዮስ 1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ የመጀመሪያ እትም፥ አዲስ አበባ (ገጽ 12)

11 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት (ገጽ 11)

12 የሐዋርያት ስራ (8:20-40)

13 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ (1927-1928ዓ. ም.) (ገጽ 89)

14 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 337)

15 Pearce, J. (2014). *Prevail: The Inspiring Story of Ethiopia's Victory over Mussolini's Invasion, 1935–1941*: New York, NY: Skyhorse Publishing. (p. 27-28)

16 *http://www.zehabesha.com/associate-professor-hassan-hussein-on-oromo-and-ethiopian-video/*

*ማህበራዊ ስነ ልቦና መሆኑ*" የተረጋገጠበት የአድዋ ድል የሁሉም የነጻነት ናፋቂ ሕዝቦች ድል ነው። ኢትዮጵያ የአድዋን ድል ለመቀዳጀት ባህላዊ የጦር መሳሪያ (ጋሻ፣ ጦርና ጎራዴን) ይዘው፣ በባዶ እግራቸው፣ በሶና ጥራጥሬ እየተመገቡ፣ በመድፍ ጭስ ታፍነው፣ በሰማይና በምድር፣ በመትረየስ በጦርና በታንክ የታጀበን፣ በሰለጠነ የጦር ሃይል የተደራጀውን ተስፋፊና ቅኝ ገዢውን የጣሊያንን ወራሪ ሃይል አንዲት አፍሪካዊት ሀገር እንዴት ልትቋቋመው ቻለች ስንል መልሱን ለማግኘት የጥንቷ ኢትዮጵያ ሕዝቧ፣ ኃይሏና ግዛቷ እንደ ሀገር ከአድዋ ድል በፊት ምን ትመስል ነበር፥ የግዛት ስፋትዋና የሕዝብዋስ ጥንካሬ እንዴት ነበር ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል።

## ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ሕዝቧ፣ ኃይሏና ግዛቷ

የጥንትዋ ኢትዮጵያ ታሪኳ የሚያሳየው ሕዝቧ ለጠላት እንደማይበገርና በየጊዜው የነገሱት ነገስታትም የሕዝቡን አንድነት ጠብቀው በየዘመናቱ የመጡባቸውን ፈተናዎች በአሸናፊነት እንደተወጡ ያሳያል። እንደቀደሙት አባቶቻቸው፣ እንደጥንት የኢትዮጵያ ጀግኖች፣ የሕዝቡ አንገዛም ባይነትና የሀገሩን ሉዓላዊነት ላለማስደፈር ካለው ቆራጥነት በተጨማሪም አጤ ምኒልክ ሕዝባቸውን በአንድነት፣ በወራሪው ጠላት ላይ እንዲነሳ ያስተባበሩበት ፈሪሃ እግዚሃብሔር የተሞላበት የክተት አዋጅና ታላቅ አመራር፣ የእቴጌዪቱም ብልሃትና አስተዋይነት የሞላባቸው ውሳኔዎች ለአድዋው ድል ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።

በሳይንስ ምርምር ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ መሆንዋ በድንቅነሽ (በሉሲ)[17] ኢትዮጵያ ውስጥ ከአፋር፣ ከደንከል የተገኘው የከርሰ ምድር ቅሪት ከሶስት ሚሊዮን ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው የሴት አጽም የሚያመለክተው የሰው ዘር በእንግሊዝኛው አጠራር *'ሆሞ ሳፒያንስ'* የተባለው ከኩሽ ምድር፥ ከኢትዮጵያ ከአፋር ተነስቶ የሰው ልጅ ምድር ላይ እንደተበተነ በመረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፥ በቅዱስ መጽሐፍም "*የኖኅ የልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው በየሕዝባቸው .... እነዚህ ናቸው። አሕዛብም ከጥፋት ውኃ በኋላ በምድር ላይ ከእነዚህ ተከፋፈሉ*"[18]ይልና ከጥፋት ውኃ በኋላ የኖኅ የልጅ ልጅ በሆነው በኩሽ ልጆች ኢትዮጵያ ትገዛ እንደነበር[19] በመሆኑም የኖኅ የልጅ ልጆች የኩሽ ነገዶች ኢትዮጵያን እንዳቀንዋትና፥ ከክርስቶስ ልደት ከአንድ ሺህ አስራ ሶስት ዓመታት በፊት ማለትም ከ(፲፻፲፫) ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ብቻ ስልሳ ስምንት (፷፰)[20] ነገስታት ኢትዮጵያ ላይ እንደተፈራረቁባት፥ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ደግሞ እስከ ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ዓመት ምህረት (፲፬፻፺፪ ዓ.ም.) ድረስ መቶ ሰማንያ ስድስት (፻፹፮) ነገስታት ኢትዮጵያን መግዛታቸውንና[21]፥ የጥንትዋ ኢትዮጵያ በጥንት ዘመን መንግስት መስርታ በራሷ ስትደዳደር የነበረች፥ ግዛትዋም እጅግ በጣም ሰፊ እንደነበር፥ በመልክዓ ምድር አቀማመጡም ከግብጽ ጋር የተያያዘና ሕዝቦቿም በንግድ ስራቸው የታወቁና የበለጸጉ፥ በሃይላቸውም የተፈሩና የተከበሩ[22] ነበሩ። የግሪክ ባለቅኔው ሆሜርም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በጉልበት ሃይለኞች እንደነበሩ ሲገልጽ፥ የምህራባውያን የታሪክ አባት የሆነው ሔሮዶተስም ኢትዮጵያውያን በሃይል ከሰዎች ሁሉ የሚበልጡ ብሎ ከመጥቀሱ ባሻገር በቅዱስ መጽሐፍ ደግሞ "*የኩሽ ልጅ .... በምድር ላይ ሃያል መሆንን ጀመረ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ ነበር*" [23] ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተተነተነበት መጽሐፍ ላይ "*ኩሽ ሁለት ስም ነበረው። ሁለተኛው ስሙ ኢትዮጲስ ይባላል። አቅኝዎቹም በአባታቸው ስም ይችን ሀገር ኢትዮጵያ ብለዋታል። በዕብራይስጥ ሙሴ ኩሽ እያለ የጠራውን በብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ...*" እንደሚል[24] ተጠቅሷል። በቅዱስ መጽሐፍም በሳይንስም ሊቀ ሊቃውንቶችና ታሪክ ጸሐፊዎች የመስከሩላት፥ የሕዝቧን አንድነት ተጎናጽፋና ተከብራ ለሃያሌ ዘመናት በራሱዋ ነገስታት ስትገዛ የኖረች፥ ኢትዮጵያ ታላቅ ጥንታዊት አፍሪካዊት ሀገር ነች።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥንት እነይሁዳ በምድረ ግብጽ በባርነት ላይ በነበሩበት ወቅት የኢትዮጵያ ነገስታት የተደላደለ መንግስት መስርተው በነጻነት ይኖሩ እንደነበር በተለያየ መንገድ በሚገባ ተዘግቧል። የኢትዮጵያ ወሰንም በምስራቅ እስከ ማዳጋስካር በሰሜን እስከ ኑብያ ዳር በደቡብ ደግሞ እስከ ኒያንዛ ባህር እንደነበርና ዛሬ የመን የሚባለው ሀገርም

---

[17] http://content.time.com/time/health/article/0,8599,1882969,00.html

[18] ዘፍጥረት (10:32)

[19] ዘፍጥረት (2:13)

[20] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 8-14)

[21] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ 1927-1928ዓ. ም. (ገጽ 40)

[22] ትንቢተ ሕዝቅኤል (29:10) ፥ ኢሳይያስ (43:3) ፥ ዜና መዋዕል 2 ካልዕ (16:8) ፥
አባ ጎርጎርዮስ1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ የመጀመሪያ እትም፥ አዲስ አበባ (ገጽ 12-14)

[23] ዘፍጥረት 10:8-9፥ አባ ጎርጎርዮስ1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያ እትም፥ አዲስ አበባ (ገጽ12)

[24] አባ ጎርጎርዮስ1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ የመጀመሪያ እትም፥ አዲስ አበባ (ገጽ 11-12)

የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር[25] ከመጠቀሱ በተጨማሪም፥

- ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሰላሳ አራት (፴፬) ዓ.ም. ኢትዮጵያን የገዛችው ንግስት ገርሳሞት ህንደኬ ሰባተኛ (፯ኛ)[26] ወሰንዋን ተሻግራ ባሁኑ ፓለስታይን በጋዛ የራሷ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሾማ እንደነበር ተጠቅሷል።
- ሌላው ደግሞ በአረብ ሀገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች በአይሁዶች ልዩ ልዩ መከራ በደረሰባቸው ጊዜ ዩስቲያኖስ የተባለው የቁስጥንጥንያ ንጉስ ለኢትዮጵያው ገዥ ለንጉስ ካሌብ እርዳታ በመጠየቅ ንጉስ ካሌብ ከአይሁዶች ጋር ተዋግቶ ድል እንዳደረገና ቤተክርስቲያንም መስርቶ ለመቶ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ስር እንደነበር የቤተ ክርስቲያኑ ፍርስራሾች እንደሚያረጋግጡ[27] ተዘርዝሯል።
- በዛጉዌ ዘመነ መንግስትም ግብጽ ከአረብ ሀገራት ጋር ጦርነት ላይ በነበረችበት ጊዜም ኢትዮጵያ የግብጽ ስደተኞችን ተቀብላ[28] በጊዜው የዛጉዌ ዋና ከተማ በነበረው በላስታ መጠለያ አግኝተዋል።

ከላይ እንደተዘረዘረው የኢትዮጵያውያን ጥንካሬና ሃይለኛነት በታሪክ የተረጋገጠ ሲሆን ወራሪው ጣሊያን ግን ይህንን ሁሉ የታሪክ እውነታ በመጣስ የቅኝ ግዛትና የመስፋፋት ህልሙን ለማሳካት ለዘመናት መንግስት መስርታ ስትተዳደር የነበረችውን አፍሪካዊት ሀገር፣ ኢትዮጵያን መውረሩ፣ ያልሰለጠነ ሀገር ላሰልጥን ብሎ መዘባበቱ ለጣሊያንንና ለተባባሪዎቹ በማያደግም ሁኔታ ለዘመናት ትልቅ ትምህርት የሰጠ ዓለም የማይረሳው ታሪክ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሃይላቸው የተፈሩና የተከበሩ እንደነበሩ፥ በንግድ ስራቸውም የታወቁና የበለጸጉ ለሌላው እርዳታ እስከመስጠት የደረሱ ቢሆኑም፥ እርዳታ እስከመስጠት የደረሰች ኢትዮጵያ ካጋጠምዋት ፈተናዎች ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከስምንት መቶ አርባ ሁለት (፰፻፵፪) ዓመተ ምህረት ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ያህል ዮዲት ጉዲት የተባለችው፣ የፈላሻዎች ንጉስ የነበረው (የጌዴዎን) ልጅ ነግሳ፣ ቤተክርስቲያኖችን በማቃጠልና ካህናትን በመግደል ያደረሰችው ጥፋትና ግራኝ አህመድ በቱርኮች ተረድቶ ኢትዮጵያ ላይ የከፈተው ከባድ ጦርነት በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያው ንጉስ አጤ ልብነ ድንግል በፖርቱጋሎች እርዳታ ግራኝን ድል ቢያደረገውም ዮዲትና ግራኝ አህመድ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ፈተናዎች እንደነበሩ በሚገባ ተመዝግበዋል።[29]

የጥንቷ ኢትዮጵያ ኃይል ከነበረበት ጥንካሬው በየዘመናቱ እየተለዋወጠ የመጣበትን ምክንያት የታሪክ ዘጋቢዎች እንደሚዘግቡልን በመተማመን ብዙ የተነገረለት የመሳፍንት ዘመን አገዛዝ ግን የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ መጥፎ አሻራ ትቶ አልፏል። ከአስራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ድረስ እንደ አውሮጳውያን ነገስታት በግዛት፣ በጥቅም፣ በዙፋን ይገባኛልና በሃይማኖት እርስ በእርሱ ብዙ ውጊያ ያደረገ የለም[30]። ልክ እንደአውሮጳውያን ነገስታትና እንደሌሎቹ በዓለም ላይ ያሉ ሀገሮች ሁሉ የኢትዮጵያ ገዢዎችም አንዱ እንዱን ለማስገበር በመሳፍንት ዘመን እርስ በአርሳቸው ብዙ ውጊያ አድርገዋል። በመሳፍንት ዘመን ሁሉም ገዢ በየአካባቢው እየነገሰ ስልጣኑን ለማደርጀትና ባላንጣውን ለመቋቋም አራሹ ገበሬን እርስ በእርሱ እያዋጋ ሌሎቹን በማስገበር አካባቢውን ይገዛ ነበር። ከአስራ ስድስተኛው ዘመን የመሳፍንት አገዛዝ በኋላ የእርስ በአርስ ጦርነት በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ መጥፎ አሻራ ትቶ ስለነበር ኢትዮጵያ ለዘመናት ወደነበረችበት አንድነት እንድትመለስና የዘመናት ታሪኳን እንደገና በማደስ፣ የተረጋጋች ሀገር ለማድረግ በአጤ ቴዎድሮስ ስርወ መንግስት ንጉሰ ነገስቱ ባላንጣዎቻቸውን በሃይል ለማሳመን ብዙ ጦርነት ተካሂዷል። ኢትዮጵያን ለሰባ ዓመታት ያናቆራትን የመሳፍንት አገዛዝ በጦር ኃይል ደምስሰው ማህከላዊ መንግስት መስርተው ኢትዮጵያ ወደ ነበረችበት አንድነት[31] ለመመለስና የመሳፍንት ዘመን የጣለውን መጥፎ አሻራ ለማደስ አጤ ቴዎድሮስ ታላቅ ተጋድሎ ያደረጉ መሪ ናቸው።

በመሳፍንት ዘመን ስልጣን የመጨበጫው ዋናው ዘዴ ውጭ ሀገር የሚሰራው የጦር መሳሪያ (ጥይት፣ ጠብመንጃና መድፍ) ነበር። ይህንንም ለማግኘት ከንጉስ ሳህለ ስላሴ ዘመን ጀምሮ ከየመንግስታቸው እየተላኩ ለንግድ፣ ሀገር ለማየት፣ አንዳንዶቹም በወንጌል መላክተኝነት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መሀል በሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት (፲፰፻፴፪) ዓ.ም.

---

[25] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) (ገጽ 3-10)

[26] የሐዋርያ ስራ (8:20-40) ፥ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.፥ ገጽ (11-12)

[27] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) ፥ (ገጽ 20)

[28] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928) ዓ.ም. ) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ.ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 30)

[29] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም. ገጽ 28)

[30] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ (ገጽ 337)

[31] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 9)

ከእንግሊዝ ቤተክርስቲያን፣ በሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አራት (፲፰፻፴፬) ዓ.ም. ደግሞ ከእንግሊዝ የንግድ ወዳጅነት ውል ለመፈጸምና ሌሎቹም ከተለያዩ መንግስታት ከሕንድ፣ ከአየርላንድ፣ ከፈረንሳይም[32] በሚላኩት አማካኝነት እያንዳንዱ ገዢ ከእነዚህ የውጭ ሰዎች ጋር በመስማማት ባላንጣውን ለማስገበር ዘመናዊ መሳሪያዎችን ያገኝ ነበር። ለምሳሌም ያህል የሸዋው ገዢ ንጉስ ምኒልክ ከጣሊያን መንግስት ጋር በመቀራረብ ዘመናዊ መሳሪያ ሲያገኙ የትግሬው ገዢ ንጉስ ዮሐንስ ደግሞ ከእንግሊዞች ጋር በመዋዋል ነበር የሚያገኙት። አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር በአስራ ስምንት መቶ አርባ ስድስት (፲፰፻፵፮) ዓ.ም. ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ የሸዋው ንጉስ ኃይለ መለኮት ሞተው ስለነበር ህጻን ልጃቸው ምኒልክን በአስር ዓመቱ አስረው[33] ወስደው አሳድገው፣ ህጻን ምኒልክ ግን ሲያድግ ጥሏቸው ወደ ወረይሙኑ ገዢዋ ወደ ወይዘሮ ወርቂት ግዛት በገባበት ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ከወይዘሮዋ ጋር ከባድ ውጊያ አድርገዋል። ንጉስ ነገስቱ ከባላንጣዎቻቸው ጋር ከሚያደርጉት የእርስ በርስ ጦርነት በተጨማሪ በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ (፲፰፻፷) ዓ.ም. በጊዜው የነበሩትን መቶ ሁለት (፻፪) የውጭ ሀገር ሰዎችን መቅደላ ላይ ሲያስሩ[34] ከታሰሩት አንዱ የእንግሊዝ ቆንስል ነበር። በመሆኑም የእንግሊዝ ጦር የአጤ ቴዎድሮስን ተቀናቃኞች በመርዳትና መኳንንቱን በመደለል ንጉስ ነገስቱ አጤ ቴዎድሮስን በቁጥጥሩ ስር ሊያደርጋቸው ስላልቻለ ለእንግሊዝ ጦር እንዲጨመርለት በጠየቀው መሰረት የሕንድ ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ሁለቱ የአጤ ቴዎድሮስ ባላንጣዎች (የትግሬው ደጃዝማች ካሳ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆነው አጤ ዮሐንስ የተባሉትና የዋጉ ደጃዝማች ጎበዜ በኋላ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አንድ (፲፰፻፷፩) ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆነው ለሶስት ዓመታት ከነገሱ በኋላ በዳጃች ካሳ የተሸነፉት) ለእንግሊዝ ጦር እርዳታ ሰጥተው እስከ መቅደላ ድረስ በመምጣት ንጉሰ ነገስቱን ሲወጉዋቸው አጤ ቴዎድሮስ ግን ለእንግሊዝ ጦር እጄን ከምሰጥ ብለው በራሳቸው እጅ ህይወታቸውን አጥፍተው ለሀገራቸው መስዋዕትነት የከፈሉ ንጉስ ናቸው።

ልክ እንደ ሁለቱ የአጤ ቴዎድሮስ ባላንጣዎች ሁሉ የሸዋውን ንጉስ አጤ ምኒልክንም አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት እንግሊዞች እርዳታ ጠይቀዋቸው ነበር። ነገር ግን ምኒልክ በአንድ በኩል እንግሊዞችና አጤ ዮሐንስ ጥሩ ግኑኝነት እንደነበራቸው ስለሚያውቁ፥ በሌላ በኩል ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ እንግሊዝን ያሸንፉ እንደሆነ እንዳይዋጉዋቸው በማሰብ፥ ነገሩን በማመዛዘን ለሁለቱም ወገኖች ወዳጅ መስለው በዝምታ ምንም መልስም እርዳታም ባለመስጠታቸው በኋላ ግን እንግሊዝ በቀጥታ አጤ ቴዎድሮስን ለማጥቃት የምኒልክን እርዳታ ስትጠይቃቸው የሰጡት መልስ "***የምትመጡት ኢትዮጵያን አስገብሮ ለመያዝ ከሆነ በነገራቹ አልስማማም***"[35] የሚል የማሻያማ ጽኑህ መልስ በሀገራቸው ሉዓላዊነት የማይደራደሩ መሆናቸውን ነው።

ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ የኢትዮጵያ ደቡባዊው ክፍል እያንዳንዱ ነገድ ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ የየራሱን ንጉስ ወይም ባላባት መርጦ እርስ በርሱ እየተዋጋም እየታረቀም በየአካባቢው በራሱ ሲተዳደር[36] ከሺህ ስምንት መቶ ስልሳ (፲፰፻፷) እስከ ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሶስት (፲፰፻፷፫) ዓመተ ምህረት ድረስ ሶስት የኢትዮጵያ ገዥዎች የትግራዩ ደጃች ካሳ ምርጫ (በኋላ አጤ ዮሐንስ የተባሉት)፣ የላስታው ዋግ ሹም ጎበዜ ገበረ መድኅንና የሸዋው ንጉስ ምኒልክ አጤ ቴዎድሮስ በጣሉት የአንድነት መሰረት ላይ ማህከላዊ መንግስት ለመመስረት በየፊናቸው መዋጋት አላቆሙም ነበር። እንደ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ አገላለጽ የአጤ ቴዎድሮስን ፈለግ በመከተል ማህከላዊ መንግስት በመመስረት ኢትዮጵያን ወደነበረችበት የአንድነት መንገድ በማህከላዊ መንግስት እንድትተዳደር ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ የንጉሰ ነገስቱን ቦታ ለመያዝና ዙፋኑን ለመውረስ ሶስቱም እርስ በእርሳቸው ከፉኛ ይሻኮቱ ነበር።

እንግሊዞቹ ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ የየአካባቢው ባላንጣዎችን በመሳሪያና በሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይደልሉ ስለነበር ለትግሬው ገዥ ለደጃዝማች ካሳ አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት ለእንግለዝ መንግስት ላደረጉት ውለታ የጦር መሳሪያ ከአሰልጣኙ ጋር ሰጥቷቸው ስለነበር በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሶስት (፲፰፻፷፫) ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የነበሩትን አጤ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው ስማቸውን ዮሐንስ ብለው በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አራት (፲፰፻፷፬) ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት ሆነው ሲነግሱ ከሶስቱ ተፎካካሪዎች ሁለቱ አጤ ዮሐንስና የሸዋው ምኒልክ ቀሩ።[37] በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ገዢዎችን በየአካባቢው መከፋፈል ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ኋላ ቀርነት በማየትና የስዊስ ቦይ መከፈቱ እንደሚጠቅመው ተረድቶ፥ ኩዲቭ ኢስማኤል የተባለው የግብጽ መሪ አውሮጳውያንን በገንዘብ ቀጥሮ፥ ኢትዮጵያን በጦር ኃይል ወርሮ፥ ግዛቱን ከሜዲትራኒያን ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ለማስፋፋት በመመኘት ሐረርን ወረረ። ግብጽ ወረራ ያካሄደውና በቀላሉ ሐረር መግባት የቻለው ኢትዮጵያ በመሳፍንት ዘመን ሁሉም በየአካባቢው ግዛቱን

---

[32] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ.ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 76)

[33] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) ፥ (ገጽ 89-92)

[34] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) (ገጽ 102-103)

[35] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 47)

[36] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 11)

[37] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 9-11)

እያጠናከረ ተከፋፍሎ በነበረበት ሰዓት የውስጥ ሃይሎች መከፋፈላቸውን ተጠቅሞ፥ በእንግሊዞችና በግብጾች ስምምነት[38] ነው። ጣሊያንም ሐረርጌን ቀድሞ ለመያዝ ብዙ ሙከራዎች አድርጎ አልተሳካለትም። ነገር ግን የግብጹ መሪ በአጤ ዮሐንስ ተቀናቃኞችም ሆነ በእንግሊዞች ግፊት ወደ ጦርነት ቢገባም ይህ ወረራ በናቀው በአጤ ዮሐንስ ጦር በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስድስት (፲፰፻፷፮) ዓ.ም. በኅዳር ወር ጉንዲት ላይ እና በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስምንት (፲፰፻፷፰) ዓ.ም. ጉርዕ ላይ ሁለት ጊዜ ተሸነፈ። ከሽንፈቱ በኋላም የእንግሊዝ መንግስት የራሱን የመስፋፋት ጥቅም በማሰብ ኢትዮጵያንና የተሸነፈውን ግብጽን በውል አስታረቀ። በውሉም ግብጽ የያዘችው የኢትዮጵያ ግዛቶች የነበሩት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ፥ ግብጾች ቱርኮችን በኢትዮጵያ ውስጥ አሳልፈው ወደ ምጽዋ ለመሰናት እንዲረዱና የአጤ ዮሐንስ መሳሪያም በምጽዋ ወደብ ያለቀረጥ እንዲያልፍ ነበር። ነገር ግን አጤ ዮሐንስ በእንግሊዝ መንግስት ተማምነው ኢትዮጵያ የተዋዋለችውን ስምምነትዋን ከፈጸመች በኋላ፥ የኢትዮጵያ ግዛቶች ሙሉ በሙሉ ሳይመለሱ፥ በእንግሊዞች ገፋፊነትና ድብቅ ዓላማ አጤ ዮሐንስ ባላሰቡት መንገድ በሺህ ስምንት መቶ ሰባት ስምንት (፲፰፻፸፰) ዓ.ም. ጣሊያን በድብቅ ምጽዋን ያዘች[39]። ምክንያቱም በሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሰባት (፲፰፻፸፯) ዓ.ም. የካቲት ሃያ ስድስት (፳፮) ቀን ጀርመን፣ በርሊን ላይ ሃያላኑ የአውሮጳ ሀገራት አፍሪካን[40] ለመቀራመት በተስማሙት መሰረት ጣሊያኖች ከሜትራድኒያን ባህር የሚዋሰኑ ሀገሮችን ለመያዝ ፈልገው ፈረንሳዮች ቀድመዋቸው አልጄሪያንና ቱኒዚያን ስለያዙ፣ ሞሮኮም ሱልጣኑ ኃይለኛ ስለነበር፣ አብዛኛው የአፍሪካ ሀገሮችም በቀጥታም በተዘዋዋሪም በእንግሊዝ ስር ስለነበሩ[41]፣ የጣሊያን ፓርላማ ቀይ ባህርን በመመኘት ጣሊያኖች አሰብን ይዘው ጣሊያንና እንግሊዝ በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አራት (፲፰፻፹፬) ዓ.ም. ጣሊያን ወደ ምጽዋ ኢትዮጵያ ጠረፍ ወታደር ልካ ለእንግሊዞች ከሱዳኖች እንድትከላከል ተስማሙ። አጤ ዮሐንስ ከእንግሊዞች ጋር ጥሩ ግኑኝነት ስለነበራቸው እንግሊዝ ይከዳኛል ብለው ባላሰቡበት ሰዓት ነበር እንግሊዞች ጣሊያንን ረድተው ምጽዋ በጣሊያን የተያዘችው። ምኒልክ ከጣሊያኖች ጋር ወዳጅ ስለነበሩ ንጉሰ ነገስቱ በምኒልክ በኩል ሳይቀር በማጠያየቅ ላይ እንዳሉ ይባስ ብሎም ኢትዮጵያ በምጽዋ በኩል ጦር መሳሪያ እንዳታስገባ ተከለከለች። ምኒልክም በአጤ ዮሐንስ ትሕዛዝ ጣሊያንን ጦርነት ፈልጋ እንደሆነ ቢጠይቁ ምላሹ ግን ልክ ንጉሰ ነገስቱ አጤ ዮሐንስ እንዳዘዙ ተደርጎ ለማታለል ሞከሩ። ለአጤ ዮሐንስም መሃዲስቶች ሀገር እንዳይዙ ልንከላከልላችሁ ነው በማለት አታለዋቸው ሸልመው ቢሸኙዋቸውም ጣሊያኖች ግን በፓርላማቸው '***የሀገር ክብር ጉዳይ ነውና የመረብ ምላሽ ገዥ ራስ አሉላ ሰሐጥን ልቀቁ ብሎናልና ሰሐጥን አንለቅም'*** ብለው ወሰኑ። የጣሊያን ፓርላማ ምጽዋ ላይ ጦር ማከማቸት የጀመረው በዶጋሊው ጦርነት ራስ አሉላ ጣሊያንን ድል በማድረጋቸው የዶጋሊን ብድር ለመመለስ ነበር። በዚህ ጊዜ ለጣሊያን ዛቻ ራስ አሉላ በእጃቸው ያሉትን አራት ጣሊያኖች አስረው ሰሐጥን በሶስት ቀን ባትለቁ እስረኞችን እገላለሁ ብለው ጣሊያንን ሲያስጠነቅቁ አጤ ዮሐንስም መቶ አምሳ ሺህ (መቶ ፶ ሺህ) ወታደሮች ይዘው ጣሊያኖችን ሊዋጉ ዘመቱ። በሰሐጥ ግን ጣሊያኖች ከምሽጋቸው ሳይወጡና ሳይዋጉ ስለቀሩ፥ መሀዲስቶች የጎጃሙን ንጉስ ተክለ ሃይማኖትን ድል በማድረጋቸው፥ ንጉሰ ነገስቱ ጣሊያንን ትተው በጎንደር የገባውን የደርቡሾች ጦር ለመውጋት ሰራዊታቸውን እየመሩ አስመራ ላይ ራስ አሉላን ሽረው ከጣሊያኖችና ከደርቡሾች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ጦርነት ገጠሙ።

ደርቡሾች ንጉስ ተክለ ሃይማኖትን ጎንደር ላይ ሲያሸንፉ የሸዋው ንጉስ ምኒልክ ጣሊያንን ለመውጋት ከሸዋ ወሎ ቢገቡም፥ ንጉሰ ነገስቱ አጤ ዮሐንስ ለጣሊያኑ በቂ ሃይል ስላለ ተጨማሪ ጦር እንደማያስፈልጋቸው በመንገር ትእዛዝ ልከው ምኒልክን ወደ ሸዋ እንዲመለሱ አዘዙ። ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ከደርቡሾች ጋር መጋፈጣቸው፥ ምኒልክም ወደሸዋ እንዲመለሱ በመታዘዛቸው፥ የደርቡሽ ጦር ጎንደርን በመዝረፍና ቀሳውስቱን በማሰቃየት ላይ ስለነበር ንጉሰ ነገስቱ ደርቡሽን ለመዋጋት ወደ መተማ ዘመቱ። የምኒልክ በጦርነቱ አለመሳተፉ ብቻ ሳይሆን ዶጋሊ ላይ ጣሊያንን ያሸነፈው ራስ አሉላንም[42] ንጉሰ ነገስቱ በመሻራቸው፥ በሰሜናዊ ምስራቅ በኩል ከጣሊያን ጋር፥ በሰሜን ምዕራብ በኩል ደግሞ ከደርቡሾች ጦር ጋር አጤ ዮሐንስ ብቻቸውን ጦርነት ስለገጠሙ በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ (፲፰፻፹፩) ዓ.ም. በጦርነት ላይ ሲዋጉ ንጉሰ ነገስቱ አጤ ዮሐንስ ህይወታቸው አለፈ[43] መስከረም ሰላሳ (፴) ቀን ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስድስት

---

38 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ (ገጽ 40)

39 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 156)

40 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 337-338) ፥ Pearce, J. (2014). *Prevail: The Inspiring Story of Ethiopia's Victory over Mussolini's Invasion, 1935–1941*: New York, NY: Skyhorse Publishing. (p. 27-28)

41 Pearce, J. (2014). (p. 27-28)

42 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 161) ፥ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም.፥ (ገጽ 383-390)

43 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም. ) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት

(፲፰፻፸፯) ዓ.ም. ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ መኩሪያም ቁጭታቸውን፥

> "*በጉንዲትና በጉንዳጉንድ፣ በጉራዕና በዶጋሊ በግብጻውያን ላይ ተደጋጋሚ ድል አድራጊነት ያገኘው የኢትዮጵያ ጦር፣ በሰለጠነውም የኢጣልያ ጦር ላይ በዶጋሊ አሸናፊነትን የተጎናጸፈው የኢትዮጵያ ጦር ድርጅታቸውና ስልጣኒያቸወ በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኘው በደርቡሽ ጦር በዚህ ጊዜ መሸነፉ ከማሳዘን አልፎ የሚያስቆጭ ነው..*" በማለት ነበር የገለጹት።

አጤ ዮሐንስ ሲሞቱ ራስ መንገሻ ዙፋኑን እንዲወርሱ በመናዘዛቸው ዙፋኑ ለራስ መንገሻ አይገባም የሚሉት ተቀናቃኝ የሆኑት የትግራይና የሀማሴን መኳንንት አካለ ጉዛይን፣ አስመራንና አካባቢዋን፣ ከርንና ቦገስን ለጣሊያን በማስረከባቸው እነሱም ከጣሊያን ጋር መስራት ስለጀመሩ ጣሊያን እነሱን መጠቀሚያ አደረጋቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በየመኳንንቱ አማካሪ መስለው የተቀመጡት ጣሊያኖችም ወዳጅ መስለው አየሰለሉ መኳንንቶችን ከማጋጨት አልፈው የጣሊያንን ድብቅ ዓላማ ያካሂዱ ነበር። ከምኒልክ ጋር የሚሰራው ኮንት አንቶኔሊ የተባለውም ለአጤ ምኒልክ ያሰበ ይመስል አጤ ምኒልክ ሀገራቸውን ለማረጋጋት እየተዘዋወሩ በነበሩት ሰዓት ወሎ ድረስ ሄዶ ውጫሌ ላይ ሰፍረው ስላገኛቸው እዚያው በጉዞዋቸው ላይ እንዳሉ ሚያዝያ ሀያ አምስት (፳፭) ቀን ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ (፲፰፻፹፩) ዓ.ም. ውል እንዲፈርሙ አደረጋቸው። ከውሉም አስራ ሰባተኛው (፲፯ኛው) አንቀጽ በአማርኛው ላይ ባለው መስልዋቸው ተፈረመ። ለአድዋው ጦርነት ምክንያት የሆነውም ውል ውጫሌ ድረስ በመሄድ በጉዞ ላይ እያሉ ያስፈረማቸው ይኸው የውጫሌ ውል አስራ ሰባተኛው (፲፯ኛው) አንቀጽ በመሆኑ በቦታው ስም የውጫሌ ውል ተብሎ ተጠራ።[44]

አጤ ዮሐንስ መተማ ዘምተው መሞታቸውን ጣሊያኖች ሲሰሙ ሰሜናዊው የኢትዮጵያን ግዛት መረብ ምላሽን ኤርትራ ብለው ሰይመው ቅኝ ግዛታቸው በማድረግ ተቆጣጠሩት። እንደ ጳውሎስ ኞኞ አጻጻፍ[45]፥

> "....*የዛሬዋን ኤርትራ ጣልያን በቅኝ ግዛትነት ሊይዙ የቻሉት ኢትዮጵያውያን መኳንንት በማህከላዊው መንግስት ላይ እየሸፈቱ ለወንድም ጠላታቸው ጠላት ለሆነው ለውጭ መንግስት በመርዳታቸው ነው። ከእነዚህም ጥቂቶቹ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሰሎሞን የአካለ ጉዛይ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ደበበ አርአያና የከረን ገዥ የነበሩትና ባላንባራስ ክፍለ ኢየሱስ ናቸው...*።
> "....*በአጤ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የኢትዮጵያ መኳንንት በስልጣን ይገባኛል ሲራኮቱ ... አጋጣሚው ይበልጥ ለጠላት አመችቶ እነሱን ጭምር በመሳሪያነት በመጠቀም ባህረ ነጋሽን ኤርትራ ብሎ በመሰየም ወደ ትግራይ ሲዘልቅ ለምኒልክ ታላቅ ራስ ምታት ሆነ።...*"

በደርቡሾችና በመሀዲስቶች መነሳት ኢትዮጵያ ባልተረጋጋችበት ወቅት የምኒልክና የዮሐንስ መከፋፈልም ለግብጹ በር ከፈተና ንጉሰ ነገስቱ አጤ ዮሐንስ ጦርነት ላይ ሲገደሉ፥ በነሐሴ አስራ ሁለት (፲፪) ቀን በሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት (፲፰፻፴፮) ዓ.ም. አያታቸው ቤት የልጆች ሞግዚት ከነበሩት ወይዘሮ እጅጋየሁ ለማ[46] ከሚባሉት የተወለዱት፥ በአጤ ቴዎድሮስ ስርወ መንግስት ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር ለጦርነት ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ የሸዋው ንጉስ ኃይለ መለኮት ሞተው ስለነበር በአስር ዓመቱ አስረው ያመጡት ህጻን ልጃቸው ምኒልክ፥ በሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ሰባት (፲፰፻፶፯) ዓ.ም. ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት ቀደም ብሎ ከታሰረበት ያመለጠው፥ በሺህ ስምንት መቶ ሰባ (፲፰፻፸) ዓ.ም. ከንጉሱ ከአጤ ዮሐንስ በተሰጣቸው ዘውድ ንጉስ የሆኑና '*ንጉሰ ነገስት ምኒልክ*' የሚል ማህተም በመጠቀም የሸዋን፣ የወሎን፣ የቤጌምድርን፣ የጎጃምንና የሳይንትን ባላባቶች በሃይልም በስምምነትም ለአስር ዓመታት የገዙት ንጉስ ምኒልክ፥[47] በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ሁለት (፲፰፻፹፪) ዓ.ም. ከአጤ ዮሐንስ ሞት በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆነው ነገሱ። አጤ ምኒልክ መላው ኢትዮጵያን በተቆጣጠሩ ጊዜ ማህተማቸው '*ንጉሰ ነገስት ምኒልክ*' መሆኑ ቀርቶ በምትኩ '*ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ*' በሚል ቀይረው መላው ኢትዮጵያን መግዛት ጀመሩ።

አጤ ምኒልክ በነገሱ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ (፲፰፻፹) እስከ ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አራት (፲፰፻፹፬) ዓ.ም. ድረስ ከጣሊያን[48] በመጡ ከብቶች ምክንያት ከባድ የከብት በሽታ ተነስቶ ለአምስት

---

ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 186) ፥ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ፥ (ገጽ 11-15)

[44] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 139-140)

[45] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ (ገጽ 138)

[46] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 11)

[47] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 89-92) ፥ ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. (ገጽ 94)

[48] Pearce, J. (2014). *Prevail: The Inspiring Story of Ethiopia's Victory over Mussolini's*

ዓመታት ያህል ታላቅ ረሀብ በመከሰቱ ከባድ የረሀብ ዘመን ነበርና ብዙ ከብቶችን በትግራይ፣ በጎጃም፣ በቤጌምድርና በላስታ ስለጨረሰ ሰዉም የሚበላው በማጣቱ ከባድ የሕዝብ እልቂት አስከተለ። ይህ ረሀብ የተከሰተው ሀገሪቱ ከነበረው የእርስ በእርስ የየአካባቢው ንጉሶች ጦርነት ፋታ አግኝተ አጤ ምኒልክ ሀገራቸውን አረጋግተው በስርዓት ለማስተዳደር በሚሯሯጡበት ጊዜ መሆኑን በርካታ ጸሐፊዎች ዘግበውታል። ከነዚህም ውስጥ የምኒልክ ጸሐፊ አለቃ ገበረ ስላሴና የጣሊያኑ መልህክተኛ ኮንት እንቶኔሊ ጥቂቶቹ ናቸው። በጽሑፋቸውም ረሀቡ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚበላ እንዳሳጣው ሰብል በመጥፋቱ የሰውም የከብትም እልቂት ማስከተሉን በዝርዝር ዘግበዋል። በሀገሪቱ የሚበላም የሚታረስም በመጥፋቱ ሕዝቡ አዲሱን የምኒልክን መንግስት እንደገደቢስ (ዕድለ ቢስ) ቆጥሮት ነበር። በተለይም በዘመነ መሳፍንት አብዛኛው ሰው ከግብርና ይልቅ ስራው ወታደርነት በመሆኑ በአጤ ቴዎድሮስና በአጤ ዮሐንስ ዘመንም ወታደሩ የባላንጣውን ከብት እየዘረፈ በማረዱ፣ በአጤ ተክለ ጊዮርጊስና በተክለሃይማኖት አገዛዝም ባላንጣዎቻቸውን ካለወታደር ማስገበር ስለማይችሉ ገበሬውን ሁሉ ጦረኛ አድርገውት ነበርና በምኒልክ ዘመን ለአምስት ዓመታት ያህል በነበረው ከባድ ረሀብ ምክንያት ንጉሱ ለጎጃሙ፣ ለወሎውና ለጎንደሩ ገዥዎች ከብት በረሀብ በማለቁ በዶማና በመጥረቢያ መኳንንቱም ሆኑ ተከታታዮቻቸው እንዲያርሱ መልህክት እንደጻፉላቸው ተጠቅሷል። ከረሀብ ዘመን በኋላ[49] የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሀብ ደቅቆ ገና ማገገም ሲጀምር ደግሞ የማይሸሸው ሌላ ሀገራዊ ችግር ገጠመው። የጣሊያን ወረራ። ከእርስ በእርስ ጦርነት በኋላ አጤ ምኒልክ ኢትዮጵያን

አረጋግተው በስርዓት ከማስተዳደር በተጨማሪም የገጠማቸውን ፈተና ጸሐፊው ጳውሎስ ኞኞ ሲገልጸው *'ታላቅ ረሀብ ተነስቶ ሕዝቡ እንደ ቅጠል ይረግፍ ነበርና ምኒልክ ጠላታቸው ጣሊያን ከያዘው በላይ እንዳያገኝ ለዋናው ጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ።'* ብሏል።

በመሆኑም ምኒልክ ለጦርነቱ ለመዘጋጀት ሲያስቡ በረሀቡ ምክንያት የሚሞተው ቀባሪ ያጣበት፣ የጋማ ከብት ስጋ የተበላበት፣ ሰራዊቱ የተመናመነበት፣ ባህላዊ መሳሪያዎችን ወይም ጊዜው ያለፈበት ዘመናዊ መሳሪያ በመጠቀም ጣሊያንን ለመከላከል አቅም የመነመነበትና ሌላው ደግሞ መኳንንቱም ተከፋፍለው በነበረበት ሰዓት በመሆኑ ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት ለጣሊያን የተመቸ ጊዜ ነበር። የራስ መንገሻ ተቀናቃኞችም ወደ ጣሊያን መግባታቸው ብቻ ሳይሆን በየአካባቢው ያሉ የመኳንንቱ ረዳት የነበሩት ጣሊያኖችም በስለላ ተጠምደው መኳንንቱን እርስ በእርስ የሚያጋጩበት ጊዜ ነበርና ራስ መንገሻም በማህከላዊ መንግስት ላለመታዘዝ በመወሰናቸው ከጣሊያኖች ጋር የተዋዋሉበት ጊዜ ነበር። አጤ ምኒልክ ይህንን ሁሉ ለማስተካከል ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው የመጀመሪያዎቹን የተወሰኑ የንግስና ዓመታት ጥሩ ግኑኝነት ለመፍጠርና ሃይል ለማጠናከር ተጠቀሙበት።

- በሶስትና በአራት የንግስና ዓመታት ከጣሊያን ጋር ያለውን ግኑኝነት እያለሳለሱ ግኑኝነታቸውን ያጠናክሩ ጀመር። ትህትና በተሞላበት መንገድ ለጣሊያን ደብዳቤ እየጻፉ ጣሊያኖችን በሁለቱም በኩል የክርስቲያን ደም መፍሰስን እንደማይፈልጉ ያሳውቁዋቸው ነበር። በተለይም ችግር ካለባችሁ ለእኔ መጻፍ ስትችሉ የዮሐንስን ሀገር መውረር ይገባ ነበርን የመንገሻን ከተማ መውረር ይገባ ነበርን ደም መፍሰስን አልወድም ብለው ጻፉላቸው።
- ሌላው ደግሞ አንዳንዶቹ መኳንንትም ተደልለው ስለነበር የተጣመመውን እያቃኑ የውስጥ ችግሮቻቸውን ሲያስተካክሉ መኳንንቶቻቸውን በዘዴ በመያዝ ማረጋጋት ጀመሩ። በአራቱ ዓመታት ጊዜ የትግራዩን ራስ መንገሻን ታረቁ፣ የጎጃሙን ተክለ ሃይማኖትን አዲስ አበባ ጋብዘው አነጋግረው በፍቅርና በደስታ ተቀብለው ታማኝነታቸውን አረጋገጡላቸው፣ ለራስ ሚካኤል ልጃቸውን ድረው አማች አደረጉዋቸው። የዋግሹም ከጣሊያኖች ጋር ስለነበር ዋግሹም ብሩን ሽረው ጓንጉልን ሾመው ግዛታቸውን ሰጡና የዋግሹም መኳንንቶች ሁሉ ከምኒልክ ጎን ቆሙ።
- አጤ ምኒልክ የውስጥ ችግሮቻቸውን እያቃለሉ በዚህ ሁሉ መሀል መሳሪያ ማደራጀታቸውን ቀጠሉ። የዉሉ አለመስተካከል ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም የአውሮጳ መንግስታት የጣሊያንን መንገድ በመቀበላቸው ክፉኛ አዝነው ምኒልክ ጣሊያኖች በሙሉ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ "*ከሀገሬ ይውጡልኝ ወደፊትም አይምጡብኝ*" ብለው ደብዳቤ ሲልኩ ጣሊያኖች ምኒልክን ለመደለል የላኩትን ሁለት ሚሊዮን ጥይት በመቀበል መታለል እንደማይችሉም በማረጋገጥ ባገኙዋቸው የጦር መሳሪያዎች ሃይላቸውን ማጠናከር ያዙ። ጣሊያኖች ሀገር ለመውረር በተዘጋጁበት ጊዜ ምኒልክ እራሳቸውን በመሳሪያም በሰው ሀይልም አጠንክረው ብርቱ ሆነው ባላቸው ሀይል ተማምነው ብልህነት የተሞላበት ዝግጅት በማድረግ ብርቱ ሆነው ቀረቡ። ያታለልዋቸውን ጣሊያኖች እያታለሉ በስነ ልቦናው የተነቃቃ ሕዝብ በማሰባሰብ፣ ጠንካራ ክንድ ያላቸው ብርቱ መሪ ለመሆን በቁ።
- ከሶስትና ከአራት የንግስና ዓመታት በኋላ ያልተከፋፈለና የተነቃቃ ሕዝብ፣ በረቀቀ ጥበብ በመሳሪያ የተደራጀ፣ በመሪው በምኒልክ ላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ ሰራዊት፣ ጠንካራ ክንድ ያለው ብርቱ መሪ ሆነው በተሻለ የጦር መሳሪያ በማደራጀትና አንዳንድ የውጭ ሀገር መንግስታትንም ወዳጅ በማድረግ ጦርነቱ ሲዳረስ የጣሊያን ወራሪነት በቀላሉ እንደማይገታ ሲያውቁ ንጉስ ነገስቱ የጦርነት ነጋሪት አስጎስመው (አዋጅ አውጀው) ለዘመቻ ተነሱ።

---

*Invasion, 1935-1941*: New York, NY: Skyhorse Publishing. (p. 27-28)

[49] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፣ (ገጽ 126-130)

የአጤ ምኒልክ ታሪካዊው አዋጅ[50]

> *አሁንም ሀገር የሚያጠፋ፣ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት፣ እግዚሃብሐር የወሰነልንን የባህር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚሃብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምኽኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሀዘንህ እርዳኝ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።*

ብለው አወጁ።

> *እግዚሃብሔር በቸርነቱ እስካሁን ድረስ ጠላት አጥፍቶ ሀገር አስፍቶ አኖረን። እኔም እስካሁን ገዛሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ስለ ሀገሬ ስለ ኢትዮጵያ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና አላዝንም። ደግሞ እግዚሃብሔር እስካሁን በጠላት ፊት አሳፍሮኝ አያውቅም ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም።* [51]

ምኒልክ ጣሊያን ጦሩን አምባላጌ ድረስ ይዞ መግባቱን ባወቁበት ጊዜ ነው ይህንን ታሪካዊ አዋጅ በማወጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር በአመራራቸው ተማምኖበት እንዲነሳ፥ በአዋጁም ምኒልክ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ልብ ውስጥ የሚገባ ጥሪ፣ ፈሪሃ እግዚሃብሔር በተሞላበት መንገድ ሕዝቡም ለዳር ድንበሩ በወራሪው ጠላት ላይ በቆራጥነት ለመነሳት የሚያደፋፍር፣ አይበገሬ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ታላቅ የአንድነት ጥሪ ነበር ያደረጉት። በእርግጥም ከምኒልክ አዋጅ እንደምንረዳው ሕዝቡ በረሃብ ምክንያት ተጎድቶ ስለነበር ምንም ምርጫ ስለሌለ ብቻ ሀገሪቱን ከወራሪው ሃይል ለመከላከል ሁሉም በቻለው መንገድ በጉልበቱም ሆነ በጸሎቱ እንዲከተላቸው እምነታቸውን በእግዚሃብሔርና በሕዝባቸው ላይ አድርገው ነበር ያወጁት። ምኒልክ የጣሊያንን የግፍ ወረራና ትዕቢት አስቀድመው የተረዱ ነበሩና ለሕዝባቸውም፣ ለሀገራቸውም ሉሃላዊነት በድፍረትና በብቃት ሕዝብን እንዲነሳ ያደረጉት የጣሊያንን የቅኝ ግዛት ህልም በቅጡ የተረዱ መሪ በመሆናቸው ነው። በእርግጥም አንዳንድ ከድቶ የነበረ ሰው ቢኖርም ከአዋጁ በኋላ ምኒልክ ላይ ሸፍተው የነበሩ እንደ ደጃማች ጓንጉል ዘገየ ዓይነቱ '***የውጭ ጠላት ስለመጣ የእርስዎና የኔ ጉዳይ ይቅር ማሩኝ መጥቼ ጠላት ልውጋ'*** በማለት ከምኒልክ ጎን በመሰለፍ ጣሊያንን ተዋግተዋል። ጣሊያኖች በትግራዩ ራስ መንገሻና በምኒልክ መሃልም ጠብ ለማጫር ራስ መንገሻን ቢያባብሉም፥ የጣሊያኖች ሀሳብ ትግራይን ለመውሰድ መሆኑን ራስ መንገሻ በተረዱ ጊዜ "***አሳባችሁ እንደዚህ ከሆነስ እኔ የዮሐንስ ልጅ ነኝና ከናንተ ጋራ ሆኜ አጤ ምኒልክን ከመውጋት አገሬንም በእናንተ እጅ ሆና ከማየት ሞት ይሻለኛል***" ከጣሊያኖች ጋር አልተባበርም በማለት በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት (፲፰፻፹፮)

ዓ.ም, ምኒልክን ምሕረት በመጠየቃቸው ከምኒልክ ጎን ጣሊያኖችን ተዋግተዋል[52]። አንዳንድ የምኒልክ መኳንንቶቻቸውም በዘመናዊ መሳሪያዎች ታጥቆ የመጣን ጣሊያንን መግጠም ከባድ እንደሆነ ሲነግርዋቸው የምኒልክ ምላሽ ግን፥

> *አንፍራ እኔ እንደሆንሁ መዝመቴን አልተውምና ስለኢጣሊያ ዘመናዊ መሳሪያና ገናናነት አትንገሩኝ። ኃይል የእግዚአብሔር ነውና እጋጠማለሁ። ብትዘምቱም ብትቀሩም ሬሳዬን ከጦር ሜዳ ፈልጉት ጠላትን በኋላ አስቀምጦ መዝመት አይቻልምና በየግዛታችሁ ያሉትን ኢጣሊያኖች*[53] *አባርሩ...*

ብለው ትህዛዝ የሰጡ ቆራጥ መሪ መሆናቸውን ነው ያረጋገጡት[54]።

## ***የክተት ዘመቻ***

ጣሊያኖች እንደርታን፣ አጋሜን፣ አክሱምንና አድዋን እንደያዙ አንዳንዶች ቁጥሩ ከሰባ እስከ ሰማንያ ሺህ ብለው ሲመዘግቡ ዌልቤ የተባለው ጸሐፊ ደግሞ ከመቶ ሺህ በላይ ሕዝብ ጣሊያንን ለመውጋትና ለሀገሩ ለመሞት እንደተነሳ

---

50 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 156-159)

51 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 234) ፥ ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. (ገጽ 156)

52 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት(ገጽ 231)

53 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) (ገጽ 222)

54 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ165)

ዘግቦታል። በመሆኑም ምኒልክ ከአዲስ አበባ በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (፲፰፻፹፰) ዓ.ም. ጥቅምት ሁለት (፪) ቀን ህጻን፣ አዋቂው፣ ቄሱ፣ አዝማሪው፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ወታደር፣ ገበሬው፣ መኳንንቱ ሳይቀር ሰራዊታቸውን አስከትለው ወደ ትግራይ ለመዝመት ጉዞ ተጀመረ። ፓውሌቲ የተባለው ጸሐፊ ጉዞውን ሲገልጸው '*ሴቶች፣ ሸማግሌዎች፣ አንካሶች፣ ቆማጣዎች፣ ሕፃናት፣ ቄሶች ሁሉ ሳይቀሩ ዳገት ሲወጡ፣ ቁልቁለቱን ሲወርዱ፣ ሸለቆውን ሞልተው በአንድነት ሲጓዙ*' መመልከቱንና ህዝቡ በሙሉ በአንድነት ተነቅሎ ለወረራ የሚሄድ ይመስላል ሲል፣ ሞልቴዶ የተባለው ጸሐፊ ደግሞ አህያው፣ በቅሎው፣ ፈረሱ፣ ሰዉ ሁሉ በአንድነት ሲጉዋዝ የጦር ወታደሮች አይመስሉም መንገዱ ሲጠብ መንገድ ይሰራሉ ማለታቸውን ጠቅሶ ጳውሎስ ኞኞ ዘግቦታል[55]።

በእርግጥም ይህ የምኒልክ ጥሪ ሕዝቡ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የስራ ዓይነትና የማህረግ ደረጃን ሳይመርጥ እንዲቀላቀላቸው ያደረጉበት የአመራር ውጤት መሆኑን በሚገባ ያረጋግጣል። በመሆኑም ለሀገር ሉሃላዊነት ለመሞት የዘመቻውን ጥሪ ተቀብለው አብሮዋቸው ሊዘምቱ ወረይሉ ድረስ ከመጡት ባላባቶች ውስጥም ሀገር እንዲጠብቁ የወላሞ (ወላይታ) ባላባት ካዎ ጦናን፣ የወሊጋ ባላባት ደጃች ጆቴን፣ የጅማው ባላባት አባ ጅፋርን፣ የሌቃ ባላባት ደጃች ገብረእግዚአብሔርን በመመደብ የመላ ሀገሪቱን መረጋጋት ያረጋገጡ መሪ ናቸው።[56] እቴጌ ጣይቱም የኢትዮጵያን ነጻነት ለመጋፋት የጣሊያኖችን በህብሪት የተሞላ የተቀነባበረ እቅድ ስለሚያውቁ ምንም ቢሆን ከዘመቻው አልቀርም ብለው የግል ሰራዊታቸውን በአዛዥ ዘአማኑኤል አስከትተው ከምኒልክ ጋር ባንድነት የዘመቱ ሴት ናቸው።

## የአምባላጌውና የመቀሌው ጦርነቶች

ከአድዋው ጦርነት በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ከጣሊያኖች ጋር በአምባላጌና በመቀሌ ሁለት ከፍ ያሉ ጦርነቶች ተካሂደዋል። የአምባላጌው ጦርነት በጣሊያን ወታደሮች ኅዳር ሃያ ስምንት (፳፰) ቀን ሲጀመር በጦርነቱም የኢትዮጵያ ሰረዊት የጣሊያንን ጦር ምሽጉ ድረስ በመሄድ ብዙ ጉዳት እያደረሰ የተናቀው የኢትዮጵያ ሰራዊት እየሞተም እየቆሰለም የጣሊያንን ጦር ከቦ መድረሻ በማሳጣቱ፥ የሚሸሽበት መንገድ እስኪያጣ ድረስ እያስጨነቀው ይህ ጦርነት የተካሄደው ገና አጤ ምኒልክ ሳይደርሱ መንገድ በጉዞ ላይ ጉሊማ የተባለው ቦታ እንዳሉ ነበር። ስድስት ቀናት የፈጀው የአምባላጌው ጦርነት ሶስት ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንና ከሺህ የሚበልጡ የጣሊያን ወታደሮች ያለቁበት ጦርነት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት በመጠናቀቁ ጣሊያን ሰራዊቱን በመቀሌ ምሽግ አከማች። የአምባላጌው ጦርነት ላይ የኢትዮጵያው ጦር የጣሊያንን ሰራዊት ምሽጉ ድረስ እየሄደ ብዙ የጣሊያን ወታደሮች በመግደሉ ጳውሎስ ኞኞ ቮልቪቼልምን[57] ጠቅሶ '*ዘመናዊ የጦር ትምህርት የሌለው*' የኢትዮጵያ ወታደር ምሽግ ውስጥ ያሉ የጣሊያን ወታደሮችን ምሽጋቸው ድረስ በመሄድ በያዘው መሳሪያ ይዋጋ እንደነበርና የጣሊያን የጦር መኮንኖችም የናቁት የኢትዮጵያ ጦር ለነፍሱ ሳይሳሳ በያዘው ጎራዴና ጦር ካሉበት ድረስ በመሄድ ስላጠቃቸው በመቀሌው ውጊያ ላይ ጣሊያኖች የውጊያውን ስልት በመቀየር ጋሊያኖ የተባለው የጦር ጀኔራል ቤተ ክርስቲያን ደፍሮ፣ ታቦት አውጥቶ፣ አጥሮ፣ ምሽጉን ድማሚት እንዲጠመድበት በማዘዝ መሽጎ፣ የመቀሌው ጦርነት ታህሳስ አስራ ስምንት (፲፰) ቀን ተጀመረ። ጣሊያኖች የኢትዮጵያ ጦር በባዶ እግሩ እንደሚዋጋ ስለሚያውቁም ምሽጋቸውን ዙሪያውን በሽቦ አጥር መከበቡ ሳያንሳቸው፥ ምድሩንም የጠርሙስ ስብርባሪ ስላነጠፉበት ፈረሰኛና እግረኛው የኢትዮጵያ ጦር ወደምሽጉ ሲጠጋ የጣሊያን ጦር በጥይት ይቀበለው ነበር። በኋላ ግን እቴጌ ጣይቱ መላ ፈጥረው የጣሊያኑ ሰራዊት ውሃ እንዳያገኝ '***ከውሃው ተኳታችሁ ዉሃ እንዳይቀዳ ጠብቁ ብለው መከሩ***'ና ጣሊያኖቹ ውሃው ይያዝብናል ብለው ስላላሰቡ አስራ አምስት (፲፭) ቀንና ሌሊት እየተዋጉ ውሃውን እንዳይቀዳ አድርገውት ጣሊያኖች በውሃ ጥም ከመሸጉበት ሊወጡና መቀሌ ላይ ሊሸነፉ የቻሉት በሴት ብልሃት ነው።

ጣሊያኖች ውሃ ጥም ሲያደክማቸው ውሃ መጠጣት የተፈቀደላቸው እርቅ ብለው በመጠየቃቸው ነው። የኢትዮጵያ ሰራዊት መቀሌ ላይ የጣሊያንን ጦር የተዋጋው ከምሽግ ሳይወጡ ነው፥ የተረፉትም ጣሊያኖች የተለቀቁት አጤ ምንክልክ ከጣሊያን ንጉስ በተጠየቁት የእርቅ ስምምነት ውል መሰረት ነበር። እርቁም የእውነት እርቅ ባለመሆኑ፥ ጣሊያኖች የመስፋፋት እቅዳቸውን ለማሳካት ነገሩን ለማጓተትና ሽንፈታቸውን ላለመቀበል፥ የኢትዮጵያን ጦር ለማዘናጋት ያደረጉት በመሆኑ ንጉሰ ነገስቱ የጣሊያን ሙከራ መስፋፋትዋን ለማጠናከር በመሆኑ፥ "*በሀገሬ በኢትዮጵያ የጣሊያንን ባንዲራ እንዲተከልበት አልፈቅድም*" ብለው በመመለስ ነው ጣሊያኖችን ያሳፈሩዋቸው።[58] የጣሊያን ጋዜጦች የዘገቡትን ጠቅሶ ጳውሎስ ኞኞ እንደጻፈው ጣሊያን ሁለት ጊዜ (አምባላጌና መቀሌ ላይ) በአፍሪካውያን መሸነፏ ውርደት በመሆኑ መቀሌ ላይ ጦርነቱ እንዳያቆም ቢገፋፋም ምድር ላይ የነበረው ሃቅ ግን የኢትዮጵያ መንግስት የጣሊያንን ጦር መፈናፈኛ በማሳጣቱ ድብቅ የእርቅ ጥያቄው የቅኝ ግዛት ማስፋፊያውን መንገድ ለማጠናከር የታሰበ ተንኮል በመሆኑ ንጉሱ አጤ ምኒልክ

---

55 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ (ገጽ160-162)

56 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ. ም.) (ገጽ 236-237)

57 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ168)

58 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ (ገጽ172-175)

ስምምነቱ የጣሊያንን ባንዲራ ለመትከል ስላልሆነ "*ግፍ የማይወደውን አምላክ ጨምሬ በመጣችሁበት መንገድ*

*አቀበላችኋለሁ"* ብለው መልሰውለት አስራ አምስት (፲፭) ቀንና ሌሊት እየተዋጉ ውሃውን እንዳይቀዳ አድርገውት ነው ጣሊያኖች በውሃ ጥም ከመሸጉበት ሊወጡና መቀሌ ላይ ሊሸነፉ የቻሉት።

## የአድዋው ጦርነት

በአድዋ ጦርነት ጊዜው የሁዳዴ ጾም ስለነበር ሰራዊቱ ራቱን በልቶ በሚቀጥለው ቀን ሳይመሽ በፊት ምንም ነገር አይበላም ነበርና ልክ ግራኝ አህመድ የተነሳ ጊዜም አጤ ገላውዲዎስ ሲዋጉ ጊዜው ጾም ስለነበረ፥ ጾሙ በአዋጅ በመሻሩ፥ ምኒልክም እንደ ግራኝ አህመድ ዘመን ጳጳሱን አቡነ ማቴዎስን ሰራዊቱ ከጦርነት በኋላ ይጹም ይፍቱት ያገኘውን እንዲበላ ቢሏቸው የጳጳሱን መልስ ጳውሎስ ኞኞ የገለጸው "*ጳጳሱ ግብጻዊ ነበሩና የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያቸው ስላልሆነ አልፈታም ብለው እምቢ አሉ። ምኒልክም እግዚሃብሔር የየዋህ አምላክ ይርዳው አሏቸው"* በማለት ነበር።

አጤ ምኒልክና ጦር ሰራዊታቸው ሀገር ለመከላከል ወደ አድዋ ጉዞ ሲጀምሩ ጥቂት መኳንንት ወደ ትግራይ ተልከው ከቻሉ የጣሊያንን ጦር እንዲወጉት ካልቻሉም እንዲጠብቋቸው በምኒልክ ታዘው ሄደው ነበር። በአጤ ምኒልክ በኩል ኢትዮጵያውያን አሰላለፋቸውን አስተካክለው ሰልፉ የተመራው በየመኳንንቱ[59] የራስ መንገሻ፣ የዋግ ሹም ጓንጉል፣ የከፋል የራስ መንገሻ፣ የራስ መኮንን፣ በከፊል የደቡብና የዋግ ሹም ጎበዜ ጦር በጄኔራል ደባ ግንባር በቀኝ በኩል፥ የወሎው፣ የአማራ ሳይንቱ፣ የሐረሩ፣ የየጁው፣ የቀኝ አዝማች ታፈሰ አባይነህና በከፊል ደቡብ የሚመራው ጦር በጀኔራል አርሞንዴ ግንባር በኩል፥ ሌላው የቀኝ አዝማች በሻህ አቦዬ የከፊል ደቡብ፣ በፊታውራሪ ገበየሁ የሚመራው የጨቦና ጉራጌው፣ በደጃዝማች ጫጫ የሚመራው የጎላ፣ በፊታውራሪ ዳምጠው የሚመራው የጊሸንና በንጉስ ተክለ ሃይማኖት የሚመራው ጦር በጀኔራል አርቤርቶኒ ግንባር በኩል፥ በንጉስ ነገስቱ፣ በእቴጌ ጣይቱ፣ የከፊል በጌምድር፣ የአፈ ንጉስ ነሲቡና በደጃዝማች ወልዴ አሻጋሪ የሚመራው የይፍራታ ጦር በደጀንነት ተሰልፎ የጠላትን ጦር በመጠባበቅ ከሰባ (፸) ሺህ በላይ ሰራዊት፥ አርባ ሁለት (፵፪) መድፎች፥ ብዛት ያላቸው ጥይቶች፥ ጦርና ጎራዴ በመያዝ የኢትዮጵያው ሰራዊት ተሰለፈ። በጣሊያኖች በኩል በቀኝ በሜጀር ጄኔራል አማኑኤል የሚመራው ግንባር፣ መካከል ላይ በሰመአታ በኩል በሜጀር ጀርኔራል አርሞንዲ የሚመራው ግንባር፣ በግራ በሜጀር ጄኔራል አርቤርቶኒ የሚመራው ግንባርና በጀኔራል ጁሽሴፔ ጋሊኖ የሚመራው ደጀን በመሆን አስራ ሰባት ሺህ[60] የሰለጠነ ዘመናዊ የጦር ሰራዊት አምሳ ስድስት (፶፮) መድፎች፣ ብዙ ሺህ ጥይቶችና ዘመናዊ ወጨፎችን በመያዝ ለጦርነት ተዘጋጀ[61]።

አድዋ ላይ ባራቲዬሪ የያዘው ምሽግ አደገኛ ቦታ ላይ በመሆኑ ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ሰራዊትን በግላጭ ለማጥቃት ስለሚመቸው በሌላ በኩል ደግሞ የሰራዊቱ ስንቅ፣ የከብቱም ቀለብ እያለቀ በመሆኑ አጤ ምኒልክ ከበው ለመቀመጥ ከሰባ ሺህ በላይ የሚጠጋው ሰራዊታቸውን የሚቀልብ ስንቅ ስለሌላቸው አጤውና ሰራዊቱን አጣብቂኝ ውስጥ ከትዋቸው ነበር። ምክንያቱም ዘማቹ ከቤቱ ከወጣ ከሰባት ወራት በላይ በማለፉ የቻለ ግማሹ በትከሻው፥ ግማሹ በአህያ በከብት የጫነው ዱቄት ጥራጥሬና በሶም እያለቀ ነበርና የፈረስና የአህያውም ቀለብ እንዲሁ እያለቀ በመሆኑ አጤ ምኒልክ በዚህ ምክንያት ሰራዊታቸውን ላለማስጨረስ ጦርነቱ ቶሎ እንዲካሄድ ፈልገው፥ ባራቲዬሪ በሰላዮቹ የኢትዮጵያውያንን እንቅስቃሴ ለማወቅ ሲሞክር ከሀገር ተወላጅ የውስጥ አርበኞች ለባራቲዬሪ የኢትዮጵያን ጦር አሳንሰው በመግለጽ፥ መኳንንቶቹም እንደታመሙ በማስመሰል፥ የራስ መንገሻ ስንቅ እንዳለቀና ንጉሱም ወደኋላ ለመመለስ አስበዋል መባሉን ባራቲዬሪ እንዲሰማ በማድረግ፥ የውሸት መረጃ በመስጠት እነባራቲዬሪ ወጥተው እንዲዋጉ የውስጥ አርበኞች አነሳስተው ጣሊያኖችን ከምሽጋቸው ወጥተው እንዲዋጉ በማድረግ አታለዋቸዋል። ባራቲዬረ ለውጊያ ሲወስንም ለአጤ ምኒልክ በውስጥ አርበኞች በኩል የባራቲዬሪ ህቅድ በምስጢር ስለደረሳቸው፥ ለመዘጋጀትም ጠቀማቸው። እነባራቲዬሪም በሰላዮቻቸው ካጣሩ በኃላ በጄኔራሎቹና በሰላዮቹ ግፊት ለጦርነት በመዘጋጀት አጤ ምኒልክ ጦርነቱን በፈለጉት መንገድ እንዲመራ በውስጥ አርበኞቻቸው፣ በሀገር ወዳድ የኢትዮጵያ ልጆች የጠላትን ዝግጅት አስቀድመው ለማወቅ አስችለዋቸዋል። ክፍተታቸውን ለማስተካከልም ጠቅምዋቸዋል። አቋማቸውን ደብቀው በሙሉ ልብ ጦርነቱን እንዲመሩም አስችለዋቸዋል። የአድዋው የመረጃ ቅብብል በተሳካ ሁኔታ የተካሄደው በብዙ የሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የነደደ የሀገር ፍቅር ስሜት ነበር።

በጣሊያኖች[62] በኩል አንዳንዶች አስራ አራት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ (፲፬የ፷፱) ብለው የዘገቡት ሌሎች ደግሞ አስራ ሰባት ሺህ ብለው የዘገቡት ነጭ ወታደሮችና አንድ ሺህ አራት መቶ (፩ ሺህ ፬ መቶ) የጭነት ከብት የሚነዱ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮችና አምሳ ስድስት (፶፮) መድፎች፣ ብዙ ሺህ ጥይቶችና ዘመናዊ ወጨፎችን ታጥቆ የካቲት ሃያ

---

[59] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ.ም. እንዳሳተሙት (ገጽ 259)

[60] https://www.youtube.com/watch?v=-FjPmCVYRvU

[61] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) ፥ (ገጽ 259)

[62] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 196-197)

ሁለት (፳፪) ቀን ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (፲፰፻፹፰) ዓ.ም. በአስራ ሁለት (፲፪) ሰዓት ሰራዊቱ ከእንኪጨው እንዳአባ ገሪማ ገባ። ሁለቱም በመጠባበቅ ላይ እንዳሉም ባራቲዬሪ ከመሸገበት ሆኖ በደረሰው የተሳሳተ መረጃ የኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች ቀለብ ሊያመጡ ሄደዋል፣ ግማሹም ታመዋል የሚለውን አምኖ የሀገሬው ሰራዊት ሀገሩን ለመከላከል ከከተመበት ስፍራ ድረስ በመሄድ መዋጋት ሲጀምር ኢትዮጵያውያን የጠላትን ጦር ከምሽቱ አምስት (፭) ሰዓት በሶስት ግንባር በጨረቃ አንደኛው ለሌላው እንዳይደረስለት በተለያየ ግንባር ከበው የጠላትን ጦር በመለያየት እንዲዳከም ከማድረግ አልፎ እንደአልቤርቶኒ ዓይነቶቹም እንዲማረኩ አድርገዋል። በእርግጥ የጣሊያን ጦር በተደጋጋሚ ከተደበቀበት ምሽግ ደፍሮ ስላልወጣ ከአንዴም ሁለቴ ጦርነት የጀመረ እየመሰለ ኢትዮጵያውያን ሲመጡበት ይሸሽና ወደ ምሽጉ ይመለስና ያናድዳቸው ስለነበር አጤ ምኒልክ "*በከንቱ ሊያሰልፈን ነው እንጂ እንደወትሮው እሱ ከሰፈሬ ድረስ መጥቶ ተኩስ ካልከፈተ አልወጣም*" ይሉ ነበርና ኢትዮጵያውያኑ ጣሊያንን ሰልለው ስላረጋገጡላቸው ንጉሱ፣ እቴጌይቱና፣ መነኮሳቱ ታቦት ይዘው በመነሳት ውጊያውም ከለሊቱ የጀመረ ጠዋት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ የአርቤርቶኒ ጦር ለቁርስ ሲበተንና ሲሸሽ፣ የአርሞዲን ምሳ ሰዓት ሲደርስ ክፉኛ እየወደቀ መሸሻ እስኪያጣ ኢትዮጵያዊው ወታደር የቀረበውን በጦር በጎራዴ እራስ እራሱን፥ የራቀውን በጠብመንጃ ጣለው። የጣሊያን ምሽግ ውስጥ የቀረው የጣሊያን ሰራዊት ምሽጉ እንዳለም መድፍ ሲለቁበት ሁለት ሺህ የሚሆን የጠላት ሰራዊት ከምሽጉ እንዲለቅ አድርገዋል።

ከምኒልክ ጋር አብረው የነበሩት ጸሐፊ ትህዛዝ ገብረ ስላሴም ስለአድዋው ጦርነት እንደተረኩት የካቲቱ ሀያ ሶስት (፳፫) ቀን የጊዮርጊስ ዕለት የጣሊያን ጦር መንቀሳቀሱን እንደሰሙ የሐረሩ ራስ መኮንን አድዋን፣ የወሎው ራስ ሚካኤል ሰላዶ ተራራን፣ የጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት የጣሊያንን ምሽግ፣ የትግራዩ ራስ መንገሻ አዲ አቡን በመያዝ፣ ራስ ዳንጉል ራስ ወሌና አጤ ምኒልክ ከኋላ ደጀን በመሆን ወታደሩ እየሸለለ እዝማሪው እያዜመ፣ መነኮሳትና ቄሶቹ በመስቀላቸው እያማተቡ ግፋ ወደፊት ሲሉ፣ የኦሮሞ ፈረሰኞች ያሉትን የዉሃ ምንጮች እየፈለጉ ከበው በመጠባበቅ ሁሉም ቦታ ቦታቸውን በተጠንቀቅ ይዘው ጠላትን ለመጋፈጥ ለጦርነቱ ሲዘጋጁ አጤ ምኒልክ እቴጌ ጣይቱ ራስ ወሌና ዋግሹም ዳንጉል በስተኋላ ደጀን በመሆን፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ የትግራይን፣ ራስ መኮንን የሐረርጌን፣ ራስ ሚካኤል የወሎን ሰራዊት አስከትለው ንጉስ ተክለሃይማኖት የጎጃሙን ጦር ፊት ለፊት ወደ ጣሊያኖች ሲያመሩ፣ ወታደሩ ለሊቱን በሙሉ ጠብመንጃውን በጫንቃው፣ ኮሮጆውን በጀርባው፣ የጥይት ከረጢቱን በቀኝ ጎኑ፣ የዉሃ ታኒካውን ከግራ ጎኑ ተሸክሞ በጭንጫና በሙቀት አቀበትና ቁልቁለት ሲወጣና ሲወርድ፣ ሲንገላታ፣ ሲደክም አድሮ ሲነጋጋ እንዳአባ ገሪማ አስር ሰዓት ገብቶ መድፉን በመጥመድ ነው ጦርነቱ የተጀመረው።[63] የፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረየሱስን መጽሐፍ ዋቢ በማድረግ ጳውሎስ ኞኞ እንደጠቀሰው ኢትዮጵያዊውም አደጋ እንደተጣለበት ባየ ጊዜ እየፈከረ፥

> *የትግሬ ነፍጠኛ፣ የሸዋ ፈረሰኛ፣ የጎጃም እግረኛ፣ የአማራ ስልተኛ ከብ ይቀላው፣ ያናፋው፣ ያንደገድገው ጀመር። ከእንዝርት የቀለለ የጁየ፣ ከነብር የፈጠነ ቤጌምድሬ፣ ከቋንጣ የደረቀ ትግሬ፣ ከአሞራ የረበበ ሸዌ፣ ከንብ የባሰ ጎጃሜ እያባረረ በየጎዳናው ዘለሰው። አውሬ የነጨው ነጭ መንጋ እየመሰለ በየዱር ሆዱን ገልብጦ ወደቀና የአሞራ ቀለብ ሆነ። የመጣው መድፍ ሁሉ ከጥይቱ ከነመንኮራኩሩ በየመንገዱ እየወደቀ ተገኘ።...እንኳን በመከራ በደስታ ቢሆን ሁለት ለሊትና አንድ መአልት ከራብና ከጥም ጋራ አይቻልም፡*
>
> *የባራቲየሪን መሸሽና የጦሩን መመታት ባየ ጊዜ ያ ሁሉ ወደኋላ የነበረ የጣሊያን መድፈኛ መጫኛውን በጎራዴ እየቆረጠ መድፉን እየጣለ በመድፉ ስፍራ እሱ እየተተካ በኢጋሰሱ እየጋለበ አስመራው ገባ። ካንድ ላይ ብቻ አስራ ስምንት (፲፰) መድፍ አንድ ጊዜ ሳይተኮስ እስከ ጥይቱ እስከ መንክራኩ ወድቆ ቀርቶ ተያዘ...*

በማለት ነው።

አለቃ ተከለ ስላሴ እንደጻፉት[64] በጦርነቱም ሃላፊውና ወታደሩ፣ ጌታና ሎሌው፣ ጭፍራው ከአለቃው ማንም ከማንም እንዳልተገናኘና ወታደሩ እሞታለሁ ብሎ ልቡ እንዳልፈራ የቆሰለውም '*በመሓይም ቃሌ ገዝቼሃለሁ ኋላ ስትመለስ ታነሳኛለህ*' ይለው እንደነበር ነው የተጠቀሰው። ኢትዮጵያዊው አስቀድሞ የተራራ ጫፍ ላይ በመውጣት የጣሊያን ጦር እየተማረከም እየወደቀም መሸሻ እስኪያጣ ድረስ ተዋግቶ ድሉ የሀገር ወዳዱ የኢትዮጵያዊ ሆነ። የጣሊያን ጦር መሸሽ ቢጀምርም ኢትዮጵያዊው ምርኮኞችንና ቁስለኞችን እየለየ ከተዋጋ በኋላ የቆሰሉትን በየድንኳኑ እያከሙና ውሃ እያጠጡ ተንከባከቧቸው። ንግስቲቱና የምኒልክ ልጅ ዘውዲቱም ለተጠማውና ለቆሰለው ውሃ ያጠጡ ጦሩንም ያበረታቱ ነበር። ድል ቢቀናም ከጦርነቱ በኋላ ብዙ መኳንንትና የኢትዮጵያ ወታደሮችም ህይወታቸውን ለሀገራቸው ስለሰው በዕለቱ ኀዘንም ነበር። በጠቅላላው ሰባት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ (፯ ሺህ ፭፻፷)[65] የጣሊያን ወታደሮች፣ ሰባት ሺህ አንድ መቶ (፯ሺህ ፩መቶ) የጣሊያን ቅኝ ግዛት ጥቁር ወታደሮች ሲሞቱ፣ አንድ ሺህ አራት መቶ ሃያ ስምንት ፲፬፻፳፰ የጠላት ወታደሮች ሲቆስሉ፣ ዘጠኝ መቶ አምሳ አራት (፱፻፶፬) የጣሊያን ወታደሮች ጠፍተዋል። አስራ አንድ (፲፩) ሺህ ጠብመንጃዎችና አምሳ ስድስት (፶፮) መድፎች ተማርከዋል። ከኢትዮጵያውያን በኩል አስር ሺህ (፲) ሲቆስሉ ሰባት (፯)ሺህ ሞተዋል[66]።

---

[63] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ. ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 208-210)

[64] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 210)

[65] https://www.youtube.com/watch?v=-FjPmCVYRvU

[66] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 211)

ኢትዮጵያውያኖች ጣሊያንን አድዋ ላይ ድል ያደረጉት የአድዋው የመረጃ ቅብብል በተሳካ ሁኔታ በአንድነትና በብዙ የሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች የነደደ የሀገር ፍቅር ስሜት የተካሄደ ስለነበር፣ የአድዋ ድል የመላው ኢትዮጵያዊ ድል ነው።

## አድዋና ሴቶች

የአድዋ ጦርነት ጾታ ወንድ ሴት አልለየም። በአድዋው ጦርነት ከየግዛቱ የተሰበሰቡ ሴቶች ከንጉሰ ነገስቱ እስከ ታችኛው ድረስ ያሉት ሁሉም ድንኳን ውስጥ ሴቶቹ ቀን በስንቅ አቀባይነትም፣ በቅስቀሳም፣ በውጊያም፣ በጦር መሪነትም ጦር መርተው ወታደር አዘው መድፍ አስተኩሰው ውጊያ አድርገዋል። ማታም ስንቅ በማዘጋጀት ሁለትዮሽ አስተዋጽዖ ነበራቸው። ከጦርነት በፊትም ሴቶቹ ከእቴጌዪቱ ጋር ወደዘመቻው የሚጓጓዝ ሸክላ፣ ምጣድ፣ አክንባሎ፣ ድስት፣ ቋንጣውን፣ በሶውን፣ ደረቅ ምግቦቹን በብዛት በማዘጋጀት፣ በጦርነቱም ሜዳ ባደሩበት ድንኳንም ሴቶች በዝግጅታቸው ለስንቅም ለዕለት ምግብም ለወጥ ለቅቤው፣ ለበርበሬው፣ ለቅመሙ፣ ለዕለት ምግብ ማዘጋጂያ ድልሁን፣ ከከፍተኛ እስከዝቅተኛ ለግብር የሚሆነውን በሙሉ እያዘጋጁ፣ ለመጠጥ ድፍድፉን ለጠላ፣ ለጠጅ የሚሆነውን ማር በማዘጋጀት ድርብ ተግባር ነበራቸው። ማታ እንጀራ ሲጋግሩ አድረው የጋገሩትን እንጀራ ያስጭናሉ፣ ከመኳንንቱም ጋር ለድርጎኛውም ለሰራዊቱም የዘማቹ ስንቅ የሚሆነውን ምግብ ወጥ ሰርተው ግብር ያዘጋጃሉ። ጠላ ቤቶችም በእንስራ ጠላቸውንና ጠጃቸውን ያቀርባሉ። እቴጌና ዘውዲቱም ለተጠማውና ለቆሰለው ውሃ ያጠጡ እቴጌዪቱም ወደ አምስት (፭) ሺህ ገደማ ሰራዊት ነበራቸውና ጦሩንም እያበረታቱ ነበር። በአድዋው ጦርነት[67] *ምንም ሴት ብሆን በዛሬ ቀን በድንኳን ውስጥ ተቀምጬ አልውልም ብለው በሰልፉ መካከል ሆነው አይዞህ በርታ"* ይሉ ነበር። የአድዋ ድል የህጻን፣ የአዋቂው፣ የሴቱም፣ የወንዱም የመላው ኢትዮጵያዊ ድል ነው።

ከድል በኋላም ምኒልክ ለሙሴ ሽፍኔ መጋቢት ሃያ ሶስት (፳፫) ቀን በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (፲፰፻፹፰) ዓ.ም. ስለአድዋ ድል የጻፉለት ደብዳቤ[68]፥

> "...*በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የህዝያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አደረግኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም....*" በማለት ነበር።

ቤርክሌይ የተባለው ጸሐፊ ደግሞ ስለአድዋ ታላቅነት የጻፈው እንዲህ በማለት ነበር።

> *"....ሃያ ሺህ ያህል ወታደሮች ያሉበት የአውሮጳ ጦር በአፍሪካ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፈ። በኔ እምነት መሰረት በዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አድዋው ያለ ጦርነት የለም። በእልቂቱ በኩል ሃያ አምስት (፳፭) ሺህ ሰዎች በአንድ ቀን ጀምበር የሞቱበትና የቆሰሉበት ነው። ፓለቲካና ታሪክ አበቃ። በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ የተወላጆች ሃይል መነሳቱ ታወቀ። የአፍሪካ ተወላጆች ታሪክ ተለወጠ። ጥቁሩ ዓለም በአውሮፓውያን ላይ ሲያምጽና ሲያሸንፍ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። አበሾች አደገኛ ሕዝቦች መሆናቸው ከአሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ተጽፎላቸዋል። የኛ ዓለም ገና ቶር እና አድዮን በሚባሉ አማልክት ሲያምን በነበረበት ጊዜ አበሾች የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበሉ ናቸው።...አሁን ሁሉንም ፍላጎት አድዋ ዘጋው ..."* ( ቤርክሌይ )

በተቃራኒው ኃያላኑ የአውሮጳ ሀገራት አንዲት አፍሪካዊት ሀገር ጣሊያንን ድል ማድረጓ ስላስደነገጣቸው፣ ሽንፈታቸውን ላለመቀበል በኢትዮጵያ ላይ የወሰኑት ውሳኔ ከሰለጠነና ካደገ ማህበረሰብ የሚጠበቅ ሳይሆን በምትኩ በኢትዮጵያ ላይ የወሰዱት እርምጃ የተዘገበው የበቀል ይመስላል፥

> *መላ እውሮጳ በምኒልክ ላይ አድሟል። አንድ ጥይት እንዳይገባ እንግሊዝና ፈረንሳይ በየቅኝ ግዛቶቻቸው በኩል ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ተስማምተዋል። በአፍሪካ ቅኝ ግዛት የነበራቸው መንግስታት በሙሉ የምኒልክን መንግስት ለማጥፋት ፕላን አውጥተዋል። ...ጥቁሮች አሜሪካን ውስጥ አፍሪካ አውሮጳን ድል አደረገች በሚል ሰልፍ በመውጣታቸው አውሮጳውያን ተባብረው የአድዋ ድል በአፍሪካም በእስያም እንዳይወራ አስከለከሉ።*[69]

---

[67] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ.ም. እንዳሳተሙት (ገጽ 256)

[68] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 159)

[69] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 226)

ምኒልክ በጊዜው ወዳጃቸው ለነበረው ለጂቡቲው ቅኝ ገዥ ለፈረንሳዊው ለሙሴ ላጋርድ መጋቢት ሃያ ሰባት (፳፯) ቀን ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት (፲፰፻፹፰) ዓ.ም. በጻፉለት ደብዳቤም

*. . .ዳሩ ግን እንደ እውነት ፍርድ ቢሆን ጣሊያኖች ከጦርነት ቢሉ ውጊያ እልፈልግኋቸውም። ከሀገሬም የመጡብኝ እነሱ። የወጉኝም እነሱ ሆነው በዚሁ ላይ ላይ መሳሪያ ሊያስከለክሉኝ ፍርድ ይሰጣቸዋል ብዬ ተስፋ አልነበረኝም። እኔ ከነጻነቴና ከወዳጅነቴ በቀር የፈለግኋቸው ነገር አልነበረኝም። ... በግፍ*

*የመጡ ሰዎች ናቸውና በጦርም በድንጋይም ቢሆን እግዚህብሔር ሳይረዳን አይቀርም። ... እኔ የክርስቲያን ደምና ገንዘብ ፈላጊ አይደለሁም። የምፈልገው የሀገሬን ነጻነት ብቻ ነው።*

በማለት ነበር።

በእርግጥም የኃያላኑ አውሮጳውያን አድማ በርሊን ላይ አፍሪካን ለመቀራመት ካደረጉት ስምምነታቸው ጋር ተመሳሳይ ይመስላል። ነገር ግን አድማው ከድል ጀምሮ ከነበር የሚያበቃበትንስ ጊዜ ተስማምተው ነበር ይሆን የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። አጤ ምኒልክ ከድል በኋላ ለተለያዩ መንግስታትም (ለሩሲያው ንጉስ ዊልያም፣ ለሮም ሊቀ ጳጳስ ሊዮን ፲፫ኛ ፣ ለእስፓኙ ንጉስ እልፎንሶ ፲፬ኛ፣ ለፖርቱጋሉ ንጉስ ለቀዳማዊ ቄርልስ፣ ለስዊስ መንግስት ርፑብሊክ ፕሬዘዳንት፣ ለቤልጅግ ንጉስ ዳግማዊ ሎዎ ፖልድ፣ ለፈረንሳይ መንግስት ፕሬዚዳንት ለሙሴ ፊሊክስ ፎርና ለሌሎችም መንግስታት) ተመሳሳይ ደብዳቤ በመላክ የጣሊያንን ወረራ በተመለከተ የተሰማቸውን በመግለጽ ጽፈው ነበር።

[70]*ኢትዮጵያ ነጻነትዋን ራስዋን የቻለች መንግስት፣ ባጠገዋም ጎረቤት የሌላት መህንዋ አስቀድሞ በአውሮጳ ነገስታት ሁሉ የታወቀ ነው። ከግራኝ ጀምሮ እስካሁን በአህዛብ እጅ ተከባ ዘወትር በጦርነት ድካም ነው ኑራችን። ከአውሮጳ ጦር መሳሪያ አመጥቼ በጦርነት ድካም ነው አሳርፋሉ ስል ከንጉስ ኡምቤርቶ አባት ጋር የፍቅርን ነገር ጀመርኩ።. . . . . . "ኮንት እንቶኔሊ የሚባል የኢጣሊያ ሰው በገንዘብህ ጠመንጃ ልግዛልዎ ቢለኝ ብዙ የዝሆን ጥርስና ወርቅ ሰጥቸው ይዞ ሄደ። . . . ጥንት ከአህዛብ ካረመኔ አገራችንን ጠብቃት የሚኖር አምላክ ከኛ ባይለይ በእግዚአብሔር ኃይል ድል አደረግኋቸው። ከዚያ ሄጀ አስመራንም የኔ ሀገር ሁሉ በሙሉ አስለቅቃለሁ ብዬ*

*ተጉዤ ሳለሁ ጀኔአራል ባልዲሴራ በጣሊያን ሰራዊት ሁሉ ላይ ተሹሜ መጥቻለሁ። ...*

*የጣሊያን ገንዘብ በላያችን ላይ የለብን፣ ለሀገራቸውም ድንበራችን የራቀ ነው። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነጻነቷን ራስዋን የቻለች መንግስት የሆነውን በተንኮል ሊወስዱት እንዴት የቻላቸዋል።"* በማለት ነበር።

*መጋቢት* ፳፫ ቀን መቀሌ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. እንቲጮ

አድዋ ላይ ኢትዮጵያን ለድል ያበቃው የሰራዊቱ፣ የንጉሰ ነገስቱና የሕዝቡ በወራሪው ጠላት ላይ በአንድነት መነሳት መቻሉ ነው። በብዙ የሀገር ውስጥ ተወላጆችና የውጭ ሀገር ሰዎች አገላላጽ የንጉሱና የንግስቲቱ ታላቅ አመራር ሕዝባቸውን በአንድነት እንዲቆም በማድረጉ ነው። አጤ ምኒልክ ጣሊያንን ለሚያህል ለገጠማቸው ጠላት ተመጣጣኝ የሆነ የሰለጠነ የጦር ኃይል ዘመናዊ መሳሪያና ወታደር ባይኖራቸውም ተፈጥሮ የቸራቸው ባህሪያቸው ለአድዋው ጦርነት ውሳኔዎቻቸው እንደጠቀማቸው ጀፍ[71] ፒርስ ሲገልጸው ምኒልክ ባይማሩም አዋቂ ብልህና ዘመናዊ ስልጣኔ ያነቃቃቸው መሪ ናቸው በማለት ነበር። ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሰዎችም ስለምኒልክ ያሉትን ጳውሎስ ኞኞም ሲጠቅስ የአድዋው ድል ምኒልክ፣

*"ብልህ፣ አርቆ አሳቢነታቸውን፣ ተጨባጭ ሁኔታ የማመዛዘንና የመገምገም ችሎታቸውን፣ የአመራር ብቃታቸውን በሚገባ አረጋግጧል።"* በሚል ብዙዎች መጻፋቸውን[72] ነው።

የታሪክ ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ደግሞ፥

---

70 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 211)

71 Pearce, J. (2014). *Prevail: The Inspiring Story of Ethiopia's Victory over Mussolini's Invasion, 1935-1941*: New York, NY: Skyhorse Publishing. (p. 27-28)

72 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. (ገጽ 141)

*"ምኒልክ በጉልበታቸውና በኃይላቸው የመመካት፣ ጦር የማጫር ሁኔታ አይታይባቸውም። ተዋግተው ካሸነፉ በኋላ በእጃቸው በወደቀው ምርኮኛ ላይ በለው፣ ቁረጠው፣ ግረፈው የሚባል የጭካኔና የዕብሪት ስራ አያሳዩም"*[73]
የሚል ነው።

የዓለም ስልጣኔ እጅግ በጣም በዝቅኝተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት በአስራ ስምንተኛው (፲፰ኛው) ክፍለ ዘመን፣ ዓለማችን ላይ በደብዳቤም ሆነ በአካል ሀሳብ ለመለዋወጥ ወራትና ሳምንታት በሚወስድበት በዚያ ዘመን የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሰዎች ምኒልክና የአድዋን ድል የገለጹበትን መንገድ በጊዜው ከወሰዱዋቸው እርምጃዎቻቸው ጋር ብናነጻጽራቸው፥

## አጤ ምኒልክ ተቀናቃኞቻቸውን የሚይዙበት መንገድ

- እንግሊዞቹ ከአጤ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ለትግሬው ገዥ ለደጃዝማች ካሳ ለእንግሊዞቹ ላደረጉት ውለታ የጦር መሳሪያ ከአሰልጣኙ ጋር ሰጥቷቸው ስለነበር ደጃዝማች ካሳ የጎጃሙን ንጉስ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አራት (በ፲፰፻፷፬) ዓ.ም. ስማቸውን አጤ ዮሐንስ ብለው በመላው ኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆነው ከነገሱ በኋላ የሸዋው ገዢ ምኒልክ የጦር ሃይላቸው ባልተደራጀበት ጊዜ አጤ ዮሐንስ ከተክለ ጊዮርጊስ የማረኩትና ከእንግሊዞቹ በስጦታ ያገኙትን መሳሪያዎች ተማምነው ሸዋን ለማስገበር ጦርነት ሲያውጁ ምኒልክ ግን አቅማቸውን በማመዛዘን ለንጉሰ ነገስቱ ለአጤ ዮሐንስ ገብተው እየገበሩ የራሳቸውን ግዛት በማጠናከር ቀስ በቀስ በብልሀት ሃይላቸውን ማደራጀት የቀጠሉ መሪ ናቸው።[74]
- በተመሳሳይ ሁኔታም የጎጃሙ ራስ አዳልን ጦር ለመግጠም ደበረ ታቦር ከገቡ በኋላ ምኒልክ ከተቀናቃኛቸው የሚበልጥ ብዛት ያለው የጦር ሰራዊት ቢይዙም ቦታውን (ዓባይ ዳር ቆላና ደጋ ዳሞትን) ራስ አዳልና ሰራዊቶቻቸው ያገሩ ተወላጆች ይበልጥ ስለሚያውቁት ለምኒልክ ግን ለጦርነት የማይመች መሆኑን በማወቅ ወደ ሸዋ የተመለሱ[75] መሪ ናቸው።
- በሌላ በኩልም ከአጤ ዮሐንስ ጋር ባላንጣነታቸው እንዳለ ሆኖ የንጉሰ ነገስቱ ታዛዥ መሆናቸውን ለማሳየት ብቻ የምኒልክ ግዛት የነበረውን የከፋን ግዛት ለጎጃሙ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት አሳልፈው እንደሰጡባቸው እያወቁ ለአዳል ንጉስ የንግስና ዝግጅት በሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሶስት (፲፰፻፸፫) ዓ.ም. የጎጃሙን ራስ አዳልን አጤ ዮሐንስ ሲሾሙ ምኒልክ ጥሪ ሲደረግላቸው የንጉሰ ነገስቱን ግብዣ ተቀብለው መሄዳቸው ተባብረው ጉዳት እንዳያደርሱባቸው ለጥንቅቄም ጭምር ነው።[76]
- ከአድዋው ጦርነት በፊት ምኒልክ የዉሉ አለመስተካከል ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም የአውሮጳ መንግስታት የጣሊያንን መንገድ በመቀበላቸው ክፉኛ አዝነው በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ጣሊያኖች በሙሉ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ "*ከሀገሬ ይውጡልኝ ወደፊትም አይምጡብኝ*" ብለው ዶክቶር ትራቬርሲ የተባለውን ሰው ደብዳቤ አስይዘው ሲልኩ የጣሊያን መንግስት ግን ምኒልክን ለመደለል ለመልህክተኛው ሁለት ሚሊዮን ጥይት በስጦታ መልክ አስይዞ ቢልከው ምኒልክ "*እናንተ ጠብ ፈለጋችሁኝ እንጂ እኔ ወዳጅነታችንን ነው የምፈልገው*" በማለት ስጦታውን

አመስግነው ተቀብለው ጣሊያኖች በሙሉ ኢትዮጵያን ለቀው እንዲወጡ ያደረጉ በስጦታው እንደማይደለሉ[77] ያስመሰከሩ ለነጮች ያልተበገሩ መሪ ነበሩ።

## ምኒልክና ሀገርንና ሕዝብን የሚመለከቱ ውሳኔዎቻቸው

- በአጤ ቴዎድሮስ ስርወ መንግስት እንግሊዞች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እንዱን ንጉስ በሌላው ላይ በማስነሳትም ሆነ መሳሪያ በመስጠት የራሳቸውን ዓላማ ያሳኩ ነበር። በአስራ ስምንት ስልሳዎቹ መጀመሪያ ላይ እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋትና እስረኞቻቸውን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ባሰቡት ጊዜ ምኒልክን ከጎናቸው እንዲሰለፉ ጠይቀዋቸው ነበር። ምኒልክ ግን ነገሩን በማመዛዘን የእንግሊዞችንና የአጤ ዮሐንስን ጠንካራ

---

[73] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 219-221)
[74] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 113) ፥ ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. (ገጽ 49-50)
[75] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) ፥ (ገጽ 107)
[76] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 65)
[77] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 113) (ገጽ 222-223)

ወዳጅነትም ስለሚያውቁ፥ አጤ ቴዎድሮስ እንግሊዝን ያሸነፉ እንደሆነም እንዳይዋጉዋቸው በማሰብም ለሁለቱም ወገኖች ወዳጅ መስለው በዝምታ ምንም መልስ ሳይሰጡ ቆይተው በኋላ ግን እንግሊዝ አጥብቃ ስትጠይቃቸው የሰጡት መልስ "*የምትመጡት ኢትዮጵያን አስገብሮ ለመያዝ ከሆነ በነገራቹ አልስማማም*"[78] የሚል የማሻያማ
ጽኑህ መልስ በሀገራቸው ሉሃላዊነት የማይደራደሩ መሆናቸውን ነው።

- በአጤ ዮሐንስ ስርወ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት እንዳይኖርና ያሉትም የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንዲጠመቁ ብለው ንጉሱ ሲያውጁ ምኒልክ ግን በተቃራነው መንገድ ነበርና የሚሰሩት በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስምንት (፲፰፻፷፰) ዓ.ም. ግብጽ ጦርዋን በአስመራ በኩል ባመጣች ጊዜ አጤ ዮሐንስ እስላሞችን እናጥፋ ብለው ቄስ ሳይቀር እንዲዘምት ባዘዙበት ጊዜ የወሎ ሕዝብ ከዮሐንስ ይልቅ እስላሙንም ክርስቲያኑንም በአንድ ዓይን በማየታቸው ለምኒልክ[79] ገብቶ ገብሯል። አጤ ዮሐንስ ፈላሻውን፣ እስላሙንና አረመኔውን(እምነት የሌለውን) በግድ ተጠመቅና ክርስቲያን ሁን እያሉ እያስገድዱ እምቢ ያለውንም በሞት
ይቀጡት ነበርና በሺህ ስምንት መቶ ሰባ (፲፰፻፸) ዓ.ም. ትህዛዛቸው፥

> "*በኢትዮጵያ ያለው እስላም ሁሉ በክርስትና እንዲጠመቅ በየአውራጃው ትሕዛዝ ስለአስተላለፉ በዚሁ በሺህ ስምንት መቶ ሰባ (፲፰፻፸) ዓ.ም. በያለበት ያለው እስላም ሁሉ በጭቃ ሹምና በመልከኛ ወደየአቅራቢያው ቤተክርስቲያን እየተነዳ በግድ እንዲቆርብ ተደረገ።*"[80]

እንደ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ገለጻ በዚሁ ምክንያት ብዙ እስላሞች ከወሎ፣ ዋጅራት፣ ራያና አዘቦ ወደ ሱዳን ተሰደው በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ (፲፰፻፹፩) ዓ.ም. አጤ ዮሐንስን መተማ ላይ በጦርነት እንደተበቀሏቸው ነው የጻፉት[81]። በተቃራኒው አጤ ምኒልክ ግን ሰው በራሱ ፈቃድ ፈልጎ ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖት መቀየርን ያስቆሙ፣ ሰራዊታቸውም በየባላገሩ ቤት እንደአጤ ዮሐንስ ሰራዊቶች እንዳይዘርፍ በአዋጅ የከለከሉ፣ ትምባሆ ማጨስም እንደማያስቀጣ በመንገር ባላገሩን ከጎናቸው እንዲቆም ያደረጉና ሕዝቡ በአጤ ዮሐንስ የተማረረባቸውን ነገሮች ያስወገዱ መሪ ናቸው።

- ልክ እንደ አጤ ዮሐንስ ምኒልክም ኢትዮጵያን አጠቃላይ መግዛት ስለነበረ ሀሳባቸው በሺህ ስምንት መቶ ሰባ (፲፰፻፸) ዓ.ም. አጤ ዮሐንስ የወሎውን ኢማም መሐመድ ዓሊን በኋላ ሚካኤል የተባሉትን ክርስትና ሲያነሱ ምኒልክ ለአጤ ዮሐንስ ታማኝ መስለው ቢገብሩም "*አንዳቸው ለአንዳቸው አልተኙም ነበርና*" ሌላውን የወሎ ኢማም አባ ዋጠውን በኋላ ኃይለ ማርያም የተባሉትን ክርስትና ከማንሳት በተጨማሪም የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተዋቸው የወሎ ገዥ በማድረግ ሚዛኑን ለመጠበቅ የሰሩ ናቸው።
- በኋላ ግን በሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስምንት (፲፰፻፷፰) ዓ.ም. ምኒልክ ክርስትና ያነሱት አባ ዋጠው በከዳቸው ጊዜ ተዋግተው ድል ካደረጉት በኋላ ወሎን በሙሉ ዮሐንስ ክርስትና ላነሱት ለመሐመድ ዓሊ (በኋላ ንጉስ ሚካኤል ተብለው ለተሰየሙት) ሰጥተው፣ ይማም ብለው ሾመው[82]፣ በሕዝብ ፊት ከወሎው ገዥ ከመሐመድ ዓሊ ጋር አብረው ተቀምጠው ሲበሉ በመታየት (በጊዜው ከእስላም ጋር መብላት እንደ ኃጢሃት ይቆጠር ስለነበር) ሰራዊቶቻቸው ቅር ቢላቸውም የወሎ ሕዝብ ግን ምኒልክን ተቀብሎ ገበረላቸው። ይልቁንም ለመሐመድ ዓሊ ያልተለመደውን እስላሙን ክርስቲያን ከሆነችው የቀድሞ ሚስታቸው የባፈናን ልጅ ወይዘሮ ማናለብሽን በማጋባት[83] የሃይማኖት ልዩነት ያልበገራቸው በሳል አመራራቸውን ያሳዩበትና ትልቅ የሀገር መሪነት ችሎታቸውን ያረጋገጡበት ወቅት ነው።
- ከአድዋ ጦርነቱ በኋላ ብዙ ሺህ የጣሊያን ምርኮኞች ስለነበሩ ጣሊያኖች እነኚህን ሁሉ ብዛት ያላቸውን ምርኮኞች ለማስለቀቅ የመጀመሪያው ሙከራቸው ምኒልክን እንታረቅ ብለው በማታለል ምርኮኞች ሊያስለቅቁና ከተለቀቁ በኋላ ጄኔራል ባልዲሴራ የተባለው ኢትዮጵያን በአዲስ መልክ ሊወጋቸው ማቀዱን በመጠርጠራቸው ምኒልክ በትዕቢትና በንቀት የተሞላውን የጣሊያንን ድፍረት ሲመልሱለት "*አዲስ ውል ተዋውለን የውጫሌ ውል መፍረሱን ለዓለም ነገስታት ሁሉ ካላሳወቃችሁ ምርኮኞችን አልለቅም*"[84] ብለው በድፍረት በመንገር ጣሊያንን መፈናፈኛ ያሳጡ መሪ እንደነበሩ ጣሊያኖችም የጻፍዋቸው መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ጣሊያን ምርኮኞችን አስለቅቆ ውጊያ የመግጠም እቅዱ

---

78 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት (ገጽ 47)
79 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 49-50)
80 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) ፥ (ገጽ 201)
81 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 201)
82 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም. የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፥ ወይዘሮ ሰናይት ተክለማርያም በ1999 ዓ. ም. እንዳሳተሙት፥ ሴንትራል ማተሚያ ቤት (ገጽ 105-107)
83 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴ፥ (1927-1928ዓ.ም.) (ገጽ 105)
84 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት፥ (ገጽ 222)

ስላልተሳከለት ሀገር ሲወረርና ንጹሃን ሲያልቁ ያላወገዙት የሮማው ጳጳስ ሊዎን አስራ ሶስተኛው (፲፫ኛው) ወራሪው ጦር ከተማረከ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈሪሃ እግዚሃብሔር ያለው መሆኑን ስለሚያውቁ ምርኮኞችን እንዲለቁ እ.ኤ.አ. በሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት (እ.ኤ.አ. በ፲፰፻፺፮) ዓ.ም. ጳጳሱ ለምኒልክ መንፈሳዊ ደብዳቤ ጻፉላቸው። ምኒልክ ግን የኢትዮጵያ ጦር ሳያገግም ምርኮኞቹን አስፈትተው ጣሊያኖች እንደገና ጦርነት ለመግጠም ማቀዳቸውን ስላወቁ ጳጳሱን በጣሊያኖችም በኩል ያለውን እንዲያስተካክሉ ጠይቀው ምርኮኞቹን ግን እንደማይለቁ በድፍረት ያሳወቁ መሪ ነበሩ።

- በመጨረሻም ጣሊያን ምርኮኞቹን ለማስለቀቅ ምኒልክ የጠየቁትን በሙሉ ለመፈጸም ሁኔታዎች ስላስገደዷት እዲስ የውጫሌውን ውል የሚሰርዝ ውልና ለጦርነቱም ካሳ የሚከፍል ተካቶበት ምርኮኞቹ እንዲለቀቁ ቢስማሙም ምኒልክ ግን በአንድ በኩል የአውሮጳ መንግስታት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሌሎቹም ማወቃቸውን ለማረጋገጥና የሚሉትንም መስማት ስለፈለጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጣሊያንም በወረቀት ፊርማ ብቻ ሳይሆነ የጣሊያን መንግስት ማህተም ያለበት እዲስ የውል ሰነድ እስኪደርሳቸው ድረስ ምርኮኞቹን ከአምስት ወራት በላይ አቆይተው የጠየቁት በሙሉ ሲሟላላቸው ምርኮኞቹን የለቀቁ ለሃያላኖቹ ነጮች ያልተበገሩ ምኒልክ ታላቅ አፍሪካዊ መሪ ነበሩ።

## ምኒልክና ስብህናቸው

ብዙዎች የምኒልክ ስብህናቸው ለአመራራቸውና ለውሳኔዎቻቸው ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል ይላሉ። ለዚህም ማሳያ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ከመጡ ተቀናቃኞቻቸው ጋር ከተዋጉ በኋላ ባላንጣዎቻቸው ተሸንፈው ሲማረኩ በምግብም በጤናቸውም እንክብካቤ ያደርጉ ነበር። ይህንን በሚመለከት ተክለጻድቅ መኩሪያ[85]ያሰፈሩትን ብናይ፥

> "*ምኒልክ በጉልበታቸውና በኃይላቸው የመመካት፣ ጦር የማጫር ሁኔታ አይታይባቸውም። ተዋግተው ካሸነፉ በኋላ በእጃቸው በወደቀው ምርኮኛ ላይ በለው፣ ቁረጠው፣ ግረፈው የሚባል የጭካኔና የዕብሪት ስራ አያሳዩም*" የሚል ነው።

- በእርግጥም በአጤ ዮሐንስ ስርወ መንግስት የጎጃሙ ነጉስ ተክለ ሃይማኖትና የሸዋው ንጉስ ምኒልክ የአጤ ዮሐንስን የአስታራቂ ሃሳብ ሳይጠብቁ ተክለ ሃይማኖት "*ከምኒልክ ጦር በፊት የኔ ጦር በወሊጋ ስለገባ፣ ክንጉሰ ነገስቱም በጎጃም ላይ የከፋ ንጉስ ተብዬ ስለተሾምሁ ከፋና አካባቢው ጉማ፣ ሊሙ፣ ከወሊጋ ጋር የኔ ግዛት ነው*" ሲሉ ምኒልክ ደግሞ "*ጎጃሞች ከአባይ ወንዝ ወዲህ ምንም ግዛት የላቸውም*" በማለት አጤ ዮሐንስ ለንጉስ ተክለ ሃይማኖት የጨመሩላቸውን የከፋ ገዢነታቸውን ስላልተቀበሉት በሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት (፲፰፻፸፬) ዓ.ም. እምባቦ ላይ ጦርነት ተደረገና ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ተሸንፈው ሲማረኩ ቆስለው ስለነበር ምኒልክ ቁስላቸውን እንደተንከባከቡላቸውና በበቅሎ ለመሄድ ስላልቻሉም በቃሬዛ "*በአልጋ ላይ አስተኝተው*" ጉዞው ወደ እንጦጦ እንደተደረገ፥ ያገሩ ባላባቶችም የተማረከውን የጎጃሙን ሰራዊት "*የቆሰለውንና የደከመውን ተቀብለው በየቤታቸው አስታመው ሲድኑ እንዲሸኙ አድርገዋል።*" በእርግጥም ተክለ ሃይማኖትን አሸንፈው ያሳዩት ርህራሄና ይልቁንም ለባላንጣቸው ያሏቸው አባባል "*እኔ ሳልፈልጋችሁ እናንተ ፈልጋችሁኝ መጣችሁ፣ እግዚአብሔር ግን በትዕቢታችሁ ጣላችሁ፣ አሁንም በየሀገራችሁ ግቡ*"[86] በማለት የተናገሩት ባህሪያቸውን በትክክል ይገልጻል። "*እምዬ ምኒልክ*" የሚለውን ቅጽል ስም ያገኙት በዚህ ስብህናቸው ይሆን?
- በአድዋው ጦርነት ላይም የጣሊያን ወታደሮች በተማረኩበት ጊዜ ምኒልክ በአዋጅ ምርኮኞችን ሰው እንዲያበላ በየመኳንንቱና በየሰው ቤት ምርኮኞችን የሰጡ ናቸው። ጳውሎስ ኞኞ ቄስ ዎርዝዊዝ የተባሉትን ጠቅሶ

እንደዘገበው ሸዋ ውስጥ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አራት (፪፰፻፷፬) ያህል ምርኮኞች እንደነበሩ መግለጻቸውንና ከጦርነቱ ጥቂት ወራቶች ቆይቶ አዲስ አበባ የመጣው ዌልዲ ደግሞ "*...ጣሊያኖቹ ምርኮኞች አራት ሺህ (፬ ሺህ) ያህል ይሆናሉ። ጣሊያን ከቅኝ ግዛቶቿ ካሰለፈቻቸው ወታደሮችም የተማረኩት*[87] *ያንኑ ያህል ይሆናሉ..*" ማለቱን አስፍሮታል። ምርኮኞችም ለመንገዳቸው ምግብና መድሃኒት ይሰጣቸው እንደነበር፣ የቆሰሉትም ወደ አዲስ አበባ የሚጓዙበት በቅሎ ሲሰጣቸው፣ ያልቆሰሉት በእግራቸው ተጉዘው አዲስ አበባ ሲደርሱ ጥሩ ኑሮ ይኖሩ እንደነበር ተዘግቧል። ምኒልክ ይህንን በማድረጋቸው የተናቀው የኢትዮጵያ መንግስት የሰለጠነ መሆኑን በስራዎቹ አስመስክረዋል።

ከአድዋ ድል በኋላም ምኒልክ ለሙሴ ሽፍኔ መጋቢት ሃያ ሶስት (፳፫) ቀን በሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት

---

[85] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 219)
[86] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ. ም. ፥ (ገጽ 219-221)
[87] ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፥ የመጀመሪያው እትም፥ ቦሌ ማተሚያ ቤት ፥ (ገጽ 225-226)

(፲፰፻፹፰) ዓ.ም. ስለአድዋ ድል የጻፉለት ደብዳቤ[88]፥

> *"...በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የህዝቢያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አደረግኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም...."*

በማለት ነበር። አጤ ምኒልክ ወራሪው ጣሊያንን የሚያህል አሸንፈው ድሉን የገለጹበት ሁኔታ ምን ያህል ፈሪሃ እግዚሃብሔር የነበራቸው እንደነበሩ ይገልጻልም በጣምም ያስደምማል።

**ማጠቃለያ**

የአድዋ ድል የመላው ኢትዮጵያዊ ድል ነው። አንዲት እፍሪካዊት ሀገር በዘመናዊ የጦር መሳሪያ በታጠቀና በሰለጠነ የጦር ሃይል የተደራጀን፣ ተስፋፊና ቅኝ ገዢ፣ የወራሪውን የጣሊያንን ሃይል በባህላዊ የእጅ ጥበበኞች ስራ በምታፈራው የጦር መሳሪያ በጦርና በጋሻ፣ በጨቤና በአንካሴ፣ በጦርና በጎራዴ በመመከት ከሙቶ ሃያ ዓመታት በፊት ዓለምን ያስደመመች፣ ምህራባውያንን ያስደነገጠች፣ ጣሊያንን ያስበረገገች፣ በርሊን[89] ላይ አውሮጳውያን አፍሪካን ለመቀራመት ያቀዱትን ዕቅድ ደጋግመው እንዲያጤኑት ያደረገች[90]፣ ብቸኛዋ በዓለም ታሪክ ጸሐፊዎችና ሊቀ ሊቃውንቶች አድዋ ላይ ድል ማድረጓ የተመሰከረላት፣ ድል የተቀናጀችበትን የድል በሃሏን ከአጋሮችዋና ከነጻነት ናፋቂው የዓለም ሕዝብ ጋር በጋራ የምታከበረው የአድዋው ድል ባለቤት፣ ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካውያን የነጻነት አርማ ስትሆን፣ "*ኢትዮጵያዊነት የዘር ሐረግ ቆጠራ ሳይሆን...ኢትዮጵያዊነት ታሪክ፣ ሕግ፣ ፍልስፍናና ማህበራዊ ስነ ልቦና መሆኑ* [91]" የተረጋገጠበት የአድዋ ድል የሁሉም የነጻነት ናፋቂ ሕዝቦች ድል ነው። ኢትዮጵያውያኖች ጣሊያንን አድዋ ላይ ድል ያደረጉት በአንድነትና በብዙ የሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች የነደደ የሀገር ፍቅር ስሜት የተካሄደ ስለነበርና ኢትዮጵያን ለድል ያበቃው ታላቅ አመራርም ኢትዮጵያውያኖችን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምህራብ እስከ ምስራቅ፥ ከዳር እስከዳር በአንድነት ማንቀሳቀስ ስለቻለም ነው።

---

88 ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም. ፥ (ገጽ 159)

89 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ1982 ዓ.ም. ፥ አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ገጽ 337-338)

90 Pearce, J. (2014). *Prevail: The Inspiring Story of Ethiopia's Victory over Mussolini's Invasion, 1935-1941*: New York, NY: Skyhorse Publishing. (p. 27-28)

91 http://www.zehabesha.com/associate-professor-hassan-hussein-on-oromo-and-ethiopian-video/